‹‹ሰው ሁሉ እናታችን ጽዮን ይላል፣
ሰው በውስጧም ተወልዷና››
መዝ.፹፮÷፭

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች
፬ መልእክት
፮ ሪፖርታዥ
፱ ቤተ አብርሃም
፲፪ ቃለ መጠይቅ
፲፭ የሕፃናት ዓምድ
፲፯ ትዝብት
፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ




## ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ


ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442
✉ 80078
አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org



ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ምኒልክ ብርሃኑ
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# የአቡነ ጎርጎሪዮስ ሥልጠና ማእከል በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ያሠለጠናቸውን ተማሪዎች አስመረቀ

*ካሳሁን ለምለሙ*

በማኅበረ ቅዱሳን ልማት ተቋማት አስተዳደር የአቡነ ጎርጎሪዮስ ሥልጠና ማእከል በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ለስድስተኛ ዙር ያሠለጠናቸውን ተማሪዎች ኅዳር ፲፱ ቀን ፳፻፲፬ ዓ/ም በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አዳረሽ አስመረቀ።

የልማት ተቋማት አስተዳደር የቦርድ ሰብሳቢ የሆኑት ዲያቆን ግርማ መታፈሪያ በምረቃ መርሐ ግብሩ ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት የመክፈቻ ንግግር የሥልጠና ማእከሉ ማኅበረ ቅዱሳን የሰጠውን የስብከተ ወንጌል የማስፋፋት ተልእኮ ለመፈጸም ትኩረት ሰጥቶ ከሚሠራባቸው የአገልግሎት ዘርፎች መካከል አንዱ የዜማ መሣሪያዎችና የልሳነ ግእዝ ቋንቋ ሥልጠናዎችን መስጠት መሆኑን ተናግረዋል።

አቡነ ጎርጎርዮስ የሥልጠና ማእከል በልማት ተቋማት አስተዳደር ሥር በ ፲፱፻፺፮ ዓ/ም የተመሠረተ መሆኑን ያስታወቁት የቦርዱ ሰብሳቢ ከምሥረታው ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ተማሪዎችን ተቀብሎ እያስተማረ ሲያስመርቅ መቆየቱን አስረድተዋል። በዛሬው የምረቃ በዓልም በበገና ፬፻፺፫ ፣ በመሰንቆ ፵፯፣ በልሳነ ግእዝ ፻፪ እንዲሁም በከበሮ ፻፩ ተማሪዎችን ያስመረቀ ሲሆን በአጠቃላይ ፯፻፵፫ ያህሉ ትምህርታቸውን በሚገባ ተከታትለው ያጠናቀቁ መሆናቸውን አክለው ገልጠዋል።

አያይዘውም የሥልጠና ማእከሉ ተጨማሪ ቅርንጫፎችን እየከፈተ መሆኑን አስረድተው በተያዘው በጀት ዓመት የሥልጠና አገልግሎቱን አጠናክሮ በመቀጠል የቤተ ክርስቲያንንና የሀገር ሀብት የሆኑ የዜማ መሳሪያዎችንና የግእዝ ቋንቋ ትምህርቶችን በስፋት እንደሚሠራ አስታውቀዋል። በዘላቂነት ተተኪ ዘማሪያንንና የዜማ መሣሪያ ተጫዋቾችን ከማፍራት አንጻር ከሥልጠና ማእከሉ ብዙ እንደሚጠበቅ በመረዳት በቀጣይ ለሥልጠናው የተለየ ትኩረት ይሰጣል ሲሉም ገልጸል።

ተመራቂ ተማሪዎች ያገኙትን ዕውቀትና ክህሎት በማሳደግ የሀገርና የቤተ ክርስቲያን ሀብት የሆኑትን ዕውቀትና ክህሎቶች የማስተዋወቅ ትልቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው የቦርዱ ሰብሳቢ ልዑል እግዚአብሔርን አጋዥ አድርገው በአገልግሎታቸው እንዲተጉ አሳስበዋል።

በመርሐ ግበሩ ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት በአዲስ አባባ ዩኒቨርስቲ የፊዚክስ ትምህርት መምህርና

በቅዱስ ያሬድና በዜማ መሣሪያዎች ላይ በርካታ ምርምር ያደረጉት ፕሮፌሰር ብርሃኑ ግዛው በበኩላቸው የቤተ ክርስቲያን



በበገና የተመረቁ ተማሪዎች በከፊል

ዜማ መሣሪያዎች ተጫዋቾችና የልሳነ ግእዝ ተናጋሪዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየመነመነ በመጣበት ወቅት የልማት ተቋማት አስተዳደር አቡነ ጎርጎርዮስ ሥልጠና ማዕከል በዘርፉ ተማሪዎችን አሠልጥኖ ማስመረቁ ችግሩን የሚያቃልል መሆኑን አስረድተዋል።

ፕሮፌሰር ብርሃኑ አያይዘውም የዜማ መሣሪያዎችና የግእዝ ትምህርቶች ሃይማኖታዊ ለዛቸውን ጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገሩ ተመራቂ ተማሪዎች ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለባቸው ጠቁመው ለዚህም ተማሪዎች የተማሩትን ዕውቀትና ክህሎት በትጋት ወደተግባር መተርጎም እንደሚገባ ተናግረዋል።

በዚህ ወቅት ሀገራችን ኢትዮጵያ በአስቸጋሪ ጦርነት ውስጥ መሆኗ በጦርነቱ ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖችና ለሀገራችን የጸሎት፣ የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባ ፕሮፌሰር ብርሃኑ አስገንዝበው ሀገራችንን ከገጠማት ፈተና ለማላቀቅ ሁሉም ዜጋ የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ አያይዘው አሳስበዋል።

ተመራቂ ተማሪዎች በዕለቱ ባስተላለፉት መልእክት በልሳነ ግእዝና በዜማ መሣሪያዎች መመረቃቸው እንዳስደሰታቸው ገልጸው የተማሩትን ሙያና ክህሎት በተግባር በመግለጥ ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር ጠቃሚ የሆነ ሥራ ለመሥራት መዘጋጀታቸውን ተናግረዋል።

# ብዙኃን መገናኛ የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ያልጠበቁ ዘገባዎችን እያስተላለፉ መሆናቸው ተገለጠ፤

በምኒልክ ብርሃኑ




*ዐውደ ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት*

ብዙኃን መገናኛ በበዓላት ወቅት በሚያስተላልፏቸው የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ፣ ሥርዐትና ትውፊት ያልጠበቁ ዘገባዎችንና መርሐ ግብሮችን እያቀረቡ መሆናቸውን ኅዳር ፲፰ ቀን፣ ፳፻፲፬ ዓ.ም በኢትዮጵያ ሆቴል በተካሔደው ዐውደ ጉባዔ ላይ ጋዜጠኛ ወ/ሮ መሠረት ከበደ ገለጡ።

ወ/ሮ መሠረት ከበደ ይህንን የገለጡት በማኅበረ ቅዱሳን አዲስ አበባ ማዕከል፣ ከሕዝብ ግንኙነት እና ዕቅበተ እምነት ክፍል ጋር በመተባበር ባዘጋጀው ዐውደ ጉባዔ ላይ "በዓልና የበዓላት አከባበር ዝግጅቶችና ዘገባ በኢትዮጵያ ብዙኃን መገናኛ አውታሮች" በሚል ርእስ ለውይይት መነሻ አሳብ ባቀረቡበት ወቅት ነው።

ባቀረቡት ጽሑፍ ላይ የብዙኃን መገናኛ የበዓል ዝግጅቶች ምን እንደሚመስሉ እና የሃይማኖት ዝግጅቶች ምን መልክ መያዝ እንዳለባቸው የጠቆሙ ሲሆን፣ አብዛኞቹ የብዙኃን መገናኛ አማራጭ የመረጃ ምንጭ እንደመሆናቸው መጠን በሚያስተላልፏቸው መርሐ ግብራት የበዓሉን መከበር ዋና ዓላማ፣ ሃይማኖታዊ ዳራና ባለታሪክን መሠረት አድርገው እንደማያከብሩና በመንፈሳዊ በዓላት አከባበር ዙሪያ ያላቸውን የዕውቀት ክፍተቶችን ገልጸዋል።

አያይዘውም ሃይማኖታዊ በዓላት የእግዚአብሔርን ሥራ በማዘከር መንፈሳዊ ሐሴትን ለማግኘት የሚከበሩ ተግባራዊ የሃይማኖት ትምህርት ቤቶች እንደመሆናቸው መጠን መንፈሳዊ ተግባራትን በመፈጸም ማክበር እንደሚገባ ጥናት አቅራቢዋ አስታውቀዋል። የብዙኃን መገናኛ ግብሮች የመንፈሳዊ በዓላትን ማኅበራዊ ፋይዳ፣ የግለሰቦች ሰብእና ቀረጻ ላይ ያላቸውን አስተዋጽኦ በሚያሳይ እና የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ለመፈጸም በሚያስችል መልኩ ከመዘጋጀት ይልቅ፤ አሰልቺ እና ቁም ነገር አልባ፣ ከበዓሉ ጋር የማይያያዙ፣ መንፈሳዊ ዐውዱንም ታሳቢ ያላደረጉ ዝግጅቶችን መሥራት ላይ ያተኩራሉ ሲሉ ወ/ሮ መሠረት ገልጸዋል።

በተለይም ቅዱስነታቸው የሚያስተላልፉትን መልእክት በመቀነጫጨብ እና ወዳልተፈለገ አቅጣጫ በመለወጥ የቤተ ክርስቲያንን መልካም ስምና ዝና በሚቀይር መልኩ የሚያቀርቡ እንዳሉ በመጠቆም፣ ብዙኃን መገናኛ ከተአማኒነትን አንጻር እውነትን መፈለግ እና መልካም ስብእናን የተላበሰ ኅብረተሰብ መቅረጽ ላይ ጠንክረው መሥራት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

በመጨረሻም የሃይማኖት በዓላት ዝግጅቶች ፈሪሃ እግዚአብሔርን ማዕከል አድርገው የሚከበሩ በመሆናቸው ምእመናንን ከሥጋዊ ደስታ ይልቅ መንፈሳዊ ሐሴትን ማግኘት እንዲችሉ፣ የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ እና ሀገራዊ ትውፊትን የጠበቁ መኾን እንዳለባቸው በመጠቆም የሚዲያ አካላት፣ ጋዜጠኞች እና ቤተ ክርስቲያን ምን ማድረግ ይገባናል? ሲሉ መድረኩን ለውይይት ክፍት አድርገዋል።

ከተለያዩ የብዙኃን መገናኛ ጥሪ የተደረገላቸው ጋዜጠኞች እና የሚዲያ ባለሞያዎች የቀረበውን ጽሑፍ መነሻ በማድረግ አስተያየቶችን የሰጡ ሲሆን፤ የብዙኃን መገናኛ ባለሞያዎቹ በዓላቱን ሃይማኖታዊ መነሻ እንዳላቸው እንደሚዘነጉ፣ የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ በሚገባ ማወቅ እንዳለባቸው፣ የተዛቡ ፕሮግራሞች ሲተላለፉ ቤተ ክርስቲያን ለምን ብሎ መጠየቅ እና በሚዲያ የመጣውን ክፍተት በሚዲያ ለመሸፈን የራሷን ብዙኃን መገናኛ ማጠንከር እንደሚገባት ተጠቁሟል።

እንዲሁም ከሚዲያ ባለቤቶች ጋር በመጣመር የበዓላት ዝግጅቶችን ማዘጋጀት፣ መረጃ አቀባዮችን በማሰናዳት የተደራጀ መረጃ መስጠት፣ የአርትዖት ሥራዎችን መሥራት፣ የቤተ ክርስቲያንን የብዙኃን መገናኛ አማካሪነት ዐቅምን ማሳደግ፣ በሃይማኖታዊ በዓላት ዝግጅት ላይ ግንዛቤ መፍጠር የሚያስችል የጋራ መድረክ እንደሚገባ በውይይቱ ተነሥቷል።

በመጨረሻም የማኅበረ ቅዱሳን አዲስ አበባ ማዕከል ምክትል ሰብሳቢ ዲያቆን ዘሪሁን ጌታነህ (ኢ/ር) ባስተላለፉት መልእክት፣ ለሁለንተናዊ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የጋዜጠኝነት ሞያ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ገልጸው የጋዜጠኞች ጉባኤ ሊኖር እንደሚገባና በቅርብ ሆኖ ያለውን ክፍተት መሙላት እንደሚቻል አሳስበዋል።

# ስለ ሰላም ጸልዩ

ሀገራችን በአሁኑ ጊዜ እያስተናገደቻቸው ካሉት ተግዳሮቶች ውስጥ አንዱ የውስጥ ሰላም እጦት ነው፡፡የሰላም ወደብ የምትባለው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሳትቀር በዚህ ዘመን በተከሠተው የሰላም መደፍረስ ምክንያት እየተናጠች ነው፡፡በተለይ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ሞት፣ ስደትና መፈናቀል ተበራክቷል፡፡ ሀገራችን ወጥቶ መግባት፣ መሽቶ መንጋት የሚናፈቅባት፣ የጥይት ድምጽ ዘወትር የሚሰማባት ሀገር ከሆነች ሰነበተች፡፡

በተለይ አንድ ዓመት ባስቈጠረው ጦርነት ከሕፃን እስከ ሽማግሌ ብዙዎች የጦርነቱ ሰለባ ሆነዋል፣ በሕይወት የተረፉት ሰላምን ፍለጋ ቤት ንብረታቸውን ጥለው ተሰደዋል፡፡በስደቱ ሳቢያ አርሰው የሚያድሩ ብዙዎች ለከፋ ረሀብ ተጋልጠዋል፤ ለሌለው የሚቆርሱ እጆች ለልመና ተዘርግተዋል፡፡ከአካባቢያቸው ርቀው በምድረበዳ፣ በየመጠለያ ጣቢያ ለመኖር ተገደዋል፡፡ባሉበት ቦታ ከረሀብ ፣ ከበሽታ እና ከእርዛት ጋር እንዲታገሉ ተገደዋል፡፡ከዚህ ሁሉ ችግር ይበልጥ የሚያሳስባቸው ደግሞ የሰላም እጦት የነገ ሕይወት ነው፡፡የቀረነውም ብንሆን በሩቅ ሆነን አንፃራዊ ሰላም ውስጥ እንደሆንን ቢሰማንም በሩቅ ስላሉት ወገኖቻችን የምንሰማው ነገር ሳይረብሸን፣ ሰላማችንን ሳይነሳን አልቀረም፡፡

ስብሐተ እግዚአብሔር የሚደርስባቸው አብያተ ክርስቲያናት፣ ገዳማት በጦርነቱ አሊያም በሰላም መታጣት ሳቢያ እየደረሰባቸው ያለው መከራ ቀላል አይደለም፡፡አብዛኛዎቹ እንዲዘጉ፣ ካህናት አገልጋዮች እንዲበተኑ ተገደዋል፡፡ አብያተ ክርስቲያናቱ በመዘጋት፣ ካህናቱ በመበተን ቢያበቃ ጥሩ ነበር አንድ ቀን ሰላም ሲሆን የተዘጉት አብያተ ክርስቲያናት ይከፈታሉ፤ የተበተኑ ካህናት ወደ አገልግሎታቸው ይመለሳሉ፡፡ችግሩ ይህ ብቻ አይደለም ዛሬ ብዙዎቹ አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎት እንዳይሰጡ ተደርገው ተቃጥለዋል፡፡ቀድሰው የሚያቈርቡ፣ ንስሐ የሚሰጡ የሚናዝዙ፣ የሚያጠምቁ ካህናት ተገድለዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያኒቱ መገልገያ ንዋየ ቅድሳቱ ሳይቀር ተዘርፈዋል፡፡የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል አይጠፋንምና ክርስቲያኖች ከልባችን ልናዝን ልንጸልይ ይገባል፡፡

ከቀዬያቸው በተፈናቀሉ የክርስቲያኖች መንደር ለብቻቸው የቀሩ አብያተ ክርስቲያናት፤ ሕፃናት፣ ወጣቶች፣ አዛውንቶች አልባ አብያተ ክርስቲያናት፤ መዝሙር የማይሰማባቸው ሰንበት ትምህርት ቤቶች፤ ቃለ እግዚአብሔር የማይነገርባቸው ዐውደ ምሕረቶች የዘወትር ሕመሞቻችን ናቸውና እግዚአብሔር በምህረት ዓይኑ እንዲጎበኘን የሰላም አምላክ ሰላሙን እንዲሰጠን በፊቱ ልንወድቅ ይገባል፡፡እኛ በሰላም ወጥተን በምንገባበት፣ ተኝተን በምንነሳበት ሁኔታ የወገኖቻችን የሰላም እጦት በእጅጉ ሊያስጨንቀን ይገባል፡፡

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ ሕፃናት በ፵ እና በ፹ ቀናቸው ሳይጠመቁ ሲቀሩ፤ ክርስቲያኖች ለንስሐ በቅተው ሥጋ ወደሙን ሳይቀበሉ ሲቀሩ ፤ፍትሃት ሳይደረግላቸው ሲቀበሩ (የመቀበር ወጉ ከደረሳቸው) የምናይበት እና የምንሰማበት ዘመን ላይ ደርሰናልና አብዝተን ልንጮኽ ይገባል፡፡እንደ ሀገር ሕፃናት ይቦርቁባቸው የነበሩ መንደሮች፣ ወጣቶች ይሠሩባቸው የነበሩ ሥፍራዎች፣ አዛውንቶች ተቀምጠው የሚያወጉባቸው ደጆች ባድማ ሆነው ማየት እጅጉን ያሳዝናል፡፡ለዚህ ሁሉ መንሥኤ ስለሆነው የሰላም መታጣት የሰላም ምንጭ እና ባለቤት የሆነው አምላካችን ለሀገራችን እና ለሕዝባችን ሰላሙን ያድል ዘንድ እያንዳንዱ ክርስቲያን ዘወትር ሊጸልይ ይገባል፡፡

የሰላም እጦት ከብዙዎች በሚነሣ ምክንያትና ውጤት ላይ ብቻ የተመሠረተ አይደለም፡፡ሰላም እያንዳንዱ ሰው ባደፈረሰው ጭጥር የሚደፈርስ እንዲሁም እያንዳንዱ ሰው ውስጣዊ ሰላሙን በጠበቀው ልክ የሚጠበቅ ነው፡፡የማኅበረሰብ ሰላም እንዲመጣ ግለሰባዊ ሰላም ሊኖር ይገባል፡፡በመሠረቱ የማኅበረሰብ ሰላም እጦት መነሻው የግለሰብ ሰላም እጦት ነው፡፡በመሆኑም ‹‹ በአንተ ታምናለችና በአንተ ለምትደገፍ ነፍስ ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ፡፡›› (ት.ኢሳ.፳፮፥፫) እንዳለ ነቢዩ እያንዳንዱ ሰው ሰላሙን ከሰላም ባለቤት ከእግዚአብሔር ዘንድ ሊፈልግ ይገባዋል፡፡እንደ ክርስቲያን

የሀገር ሰላም መደፍረስ የሚያሳስበን፣ የክርስቲያኖች፣ የአብያተ ክርስቲያናት ሰላም መታጣት የሚቈረቍረን ልንሆን ይገባል፡፡

ይህም የሚሆነው ስለሰላም በየዐደባባዩ በመናገር፣ በየማኅበራዊ ሚዲያው በመጻፍ፣ የነጭ ርግብ ምስል በጨርቅ ላይ በመሳልና በማውለብለብ ብቻ ሳይሆን በሰላም በመኖር፣ ስለሰላም በመጸለይ ሊሆን ይገባል፡፡ከግለሰብ የሚነሣ የሰላም እጦት የሚዘልቀው የሀገር ሰላም እጦት ድረስ ነውና በቤታችን፣ በጎረቤታችን፣ በአካባቢያችን ሰላም እንዲሰፍን አጥብቀን ልንሠራ፣ የሰላም ባለቤት ሰላምን እንዲሰጠን በእምነት ወደ እግዚአብሔር መጸለይ ለእኛ ለክርስቲያኖች ተገቢ ብቻም ሳይሆን ግዴታም ጭምር ነው፡፡ምክንያቱም ውጫዊ ሳይሆን ውስጣዊ፣በግለሰቦች ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን እግዚአብሔር የሰጠን፣ ምክንያቱም ሰላም በጦርነት ብቻ ሳይሆን በጸሎት የሚመጣ ነውና ይልቁንም በዚህ የጾም ወቅት ክርስቲያኖች ሁላችን በጸሎታችን መሀል ሰላምን ፍለጋ ስለተሰደዱት ወገኖች፣ የሰላም እጦት ማዕበል ስለሚንጣት ሀገራችን ጭምር አጥብቀን ልንጸልይ ይገባል፡፡

ለሕዝቦቿ፣ ለሀገር፣ ለመሪዎቿና ለሠራዊቷ ሳይቀር ዘወትር በቅዳሴዋ የምታውጀው፣ ስለሰላም የምትጸልየው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ዛሬ በሰላም መታጣት የተነሣ ታውካለችና ስለእርስዋ ግድ ሊለን አብዝተን ልንጸልይ ከእያንዳንዳችን የቤተ ክርስቲያን ልጆች ይጠበቃል፡፡‹‹ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፥ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም›› (ዮሐ. ፲፬፥፳፯) እንዳለ ሰላም ጊዜያዊ ያይደለ ዘለቄታዊ የእግዚአብሔር ስጦታ ነውና ወደ ሰጪው የሰላም አለቃ ወደ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጸለይ ተገቢ ነው፡፡

ብዙዎች በሰላም መታጣት ምክንያት ዋጋ እየከፈሉ ባሉበት በዚህ ወቅት በሕዝባችን፣ በቤተ ክርስቲያናችን እና በሀገራችን የመጣውን ይህን የሰላም መቅሰፍት ያርቅልን ዘንድ እንደ ክርስቲያን ልንኖር፣ የቃል ብቻ ሳይሆን የተግባር ሰው መሆን ይጠበቅብናል፡፡ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሰላም መርከብ፣ ክርስትና ሰላም ነውና በዚህ ብዙ ነገር ምስቅልቅሉ በወጣበት ዘመን ከእኛ ብዙ ይጠበቃል፡፡‹‹ሰላምን እሻ ተከተላትም›› እንዳለ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ(ሮሜ.፲፪፥፲፬) እግሮቻችን ወደ ሰላም የሚፈጥኑ፣ አንደበቶቻችን ሰላምን የሚሰብኩ፣ ልቦቻችን ስለሰላም የሚጸልዩ ሊሆኑ ይገባል፡፡በአጠቃላይ በመስቀሉ ሰላም የተደረገልን እኛ ክርስቲያኖች ስለሰላም መስፈደን ትልቁን ድርሻ ልንወስድ ይገባል፡፡

**አብያተ ክርስቲያናቱ በመዘጋት፣ ካህናቱ በመበተን ቢያበቃ ጥሩ ነበር አንድ ቀን ሰላም ሲሆን የተዘጉት አብያተ ክርስቲያናት ይከፈታሉ፤ የተበተኑ ካህናት ወደ አገልግሎታቸው ይመለሳሉ፡፡ ችግሩ ይህ ብቻ አይደለም ዛሬ ብዙዎቹ አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎት እንዳይሰጡ ተደርገው ተቃጥለዋል፡፡ቀድሰው የሚያቈርቡ፣ ንስሐ የሚሰጡ የሚናዝዙ፣ የሚያጠምቁ ካህናት ተገድለዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያኒቱ መገልገያ ንዋየ ቅድሳቱ ሳይቀር**

# ሐሰተኞች አጥማቂዎችና የቤተ ክርስቲያናችንንና የምእመናን ፈተናዎች

## •አጥማቂስ ማን? ስለጥምቀት ቤተ ክርስቲያን ምን ታስተምራለች? መጻሕፍትስ ምን ይላሉ?

በሻምበል ጥላሁን

ክፍል አንድ

አሁን ባለንበት ዘመን በተደጋጋሚ ከሚነሡ ጥቄዎች እና የቤተ ክርስቲያን ፈተናዎች መካከል አንዱ የጥምቀትና አጥማቂዎች ጉዳይ ነው። ጥምቀት ስንል (የ፵ እና የ፹ ጥምቀትን አይመለከትም) በብሉይና በሐዲስ ኪዳን ምእመናን ፈውሰ ሥጋ ፈውሰ ነፍስ እንዲያገኙባቸው ከእግዚአብሔር ከተሰጡ ጸጋዎች አንዱ ነው። (፪ኛ ነገሥት ፭፤ ዮሐ. ፭፣ዮሐ. ፱)። በቤተ ክርስቲያን ታሪክም ውስጥ በልዩ ልዩ ገድላት ላይ እንደምናነበው እግዚአብሔር አምላክ በጠበል ሕዝቡን ሲፈውስ ኖሯል። ሕዝብ ፈውስ የሚያገኝባቸው እንደ ስሊሆምና እንደ ቤተ ሳይዳ የታወቁ የቃል ኪዳን ቦታዎችም ነበሩ።

ስንዱዋ ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ መፈሳዊ ሀብቷ ምእመናንን ከደዌያቸው ፈውሳቸዋለች፣ ዐይነ ሥውራንን አብርታለች፣ ሽባ የነበሩትን ተርትራለች፣ በዓለም ጥበብ መፍትሔ ያጡትን፤ ከዓለም ጥበብ በላይ በሆነ ማዳንም ከአካላቸው እባብ፣ እንቁራሪት፣ ወፍ የወጣላቸው……ወዘተ ብዙ ተአምራትና የመዳን ውለታ የተዋለላቸው ምእመናን እጅግ በርካታ ናቸው።

አሁን በያዝነው ዘመን አያሌ ‹አጥማቂ ነን› የሚሉ ሰዎች ተነሥተዋል። ክብራቸውን የሚገልጥ ማስታወቂያ ያስነግራሉ፣ መቍጠሪያ ይሸጣሉ፣ ቅባት ይቀባሉ፣ አዳራሽ ከፍተው ወይም ሕዝብ በሜዳ ሰብስበው እንፈውሳለን ይላሉ፤ ሰይጣን ተናገረ የሚባለውን በካሴት ቀድተው ይሸጣሉ። እነዚህ ‹አጥማቅያን ነን› ባዮች አዳራሽ ከፍተው፣ ሜዳ ሰብስበው ከመሥራት አልፈው "ሕጋዊያን ሆነው" በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን በመግባት ይህንኑ እኩይ ተግባር በኩራት እየፈጸሙ ይገኛሉ። በዚህም ብዙ ቤተሰብ በትነዋል፣ አባትና ልጅ እኅትና ወንድም አቆራርጠዋል። እነዚህ "አጥማቅያን" የራሳቸው አሠራር ያላቸው ሲሆን፤ የሚጠብቃቸው ጠባቂ (ጋርድም) ቀጥረው የሚንቀሳቀሱ ናቸው። እነዚህ "አጥማቅያን"ን የሚያጠምቁበት ደብር ያለ አገልጋይ ከተቃወማቸው ተቃዋሚውን በጠባቂዎቻቸው ከማስደብደብ አልፈው በረዥሮም እጃቸው ከኖረበት ደብርም ያስቀይሩታል። ተቃዋሚው የአጥቢያው ምእመን ከሆነ ደግሞ ርኩስ መንፈስ አደረበት የተባለ ሰው የዚያን ሰው ስም ወይም የቤተሰቡን ስም እንዲያጠፋ ይደረጋል። በነዚህ "አጥማቅያን" የበርካቶች ምእመናን ቤቶች ፈርሰዋል። በ"አጥማቂዎቹ" አማካይነት ለጥምቀት የሚሰበሰቡ ሰዎች አብዛኞቹ ይጮኻሉ። ሁሉም በሰይጣን ተይዘዋል ይባላሉ፣ ሁሉም ድግምት፣ መተት፣ መድኃኒት፣ ጥንቆላ እንደተደረገባቸው ይነገራቸዋል። ሰይጣንን አምነው ከባሎቻቸው፣ ከሚስቶቻቸው፣ ከእኅት ወንድሞቻቸው፣ ከጎረቤቶቻች፣ ከሥራ ባልደረቦቻቸው ይጣላሉ።ከባቴ አበሳነትን ፈጽሞ የረሳ፣ ከፍቅር ይልቅ ጠላትነትን ለማስፈን የመጣ፣ ሰዎች እግዚአብሔርን አምነው ከመፋቀር ይልቅ እሱን አምነው እንዲጣሉ የሚያደርግ የሰይጣን አሠራር ነው።

የሰይጣንን ምስክርነት አምነው ፴ ዓመታት ከኖሩትና ከመሩት ትዳር የተፋቱ፣ ከአንድ ማሕጸን የወጡ ወንድማማቾች የተለያዩበት፣ ከ፳ ዓመት በላይ በመዋደድ በእጮኝነት ኖረው የተለያዩ ወዘተ….. በርካቶች ናቸው። በቤተ ክርስቲያናችን ይህ አሠራር የክርስቶስን ነገረ ድኅነት የሚፃረርና ከማዳን ሥራውም የወጣ ነው። ከክርስቶስ ክብርና ኃይል ይልቅ የሰይጣንን ኃይል ለማሳየት የሚሠራም ነው። ከዚህ ቀጥለን በምናቀርባቸው ተከታታይ ዘገባዎች ስለ ሐሳዊያኑ አጥማቅያን መግለጫዎችን ጨምሮ አጥማቂ ማን ነው?፣ ለመሆኑ ስለጥምቀት ቤተ ክርስቲያን ምን ታስተምራለች? መጻሕፍትና ሊቃውንቱስ ምን ይላሉ? የሚለውን ሐሳብ በዝርዝር እናያለን። ከዚህ በታች በነዚህ "አጥማቅያን" ሰበብ የተናጋ ቤተሰብን ታሪክ እናያለን።

ወለተ ጊዮርጊስ (ለባለታሪካችን ደህንነት ስንል የተጠቀምነው የክርስትና ስሟን ነው) በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አማኑኤል ወይም በተለምዶ እህል በረንዳ አካባቢ ትኖራለች፤ ወለተ ጊዮርጊስ አንዲት ሴት እኅትና ሦሥት ወንድሞች አሏት። ባለ ታሪካችን በ፳፻፬ ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ንግድ ሥራ ኮሌጅ በአካውንቲንግ ተመርቃ በአንድ የመንግሥት ድርጅት ውስጥ ተቀጥራ እንደምትሠራ ትናገራለች። ለሷ ከዚህ መድረስ የቤታቸው የኢኮኖሚ ማገር የሆነው የታላቅ ወንድሟ ድጋፍ ተጠቃሽ ነው።ታላቅ ወንድሟ ከሷም ውጪ ቤቱን የማስተዳደር ኃላፊነቱ ከእሱ ላይ ስለወደቀ እሷን ጨምሮ ሁሉንም አስተምሮ ሥራ ማሲያዙን ታስረዳለች።

በቤታቸው ጠብ፣ ኩርፊያም ሆነ ንትርክና ጭቅጭቅ የለም፤ ሁላችንም አንቺ ትብስ እኔ እብስ እየተባባልን ነው ያደግነው።በኛ መከባበር የማይቀና የሰፈር ሰው አልነበረም።ልጆች ማለት እንደ ወለተ ጊዮርጊስ ቤተሰቦች ነው እየተባለ በየቦታው ይነገር ነበር። ታዲያ የመልካም ነገር ሁሉ ፀር የሆነው ሰይጣን ይሄን ታላቅ ቤተሰብ በጠበጠ። ያ ሁሉ ደስታ ከቤታችን ራቀ፣ መከባበር ከመካከላችን ጠፋ፣ አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ የምንባባለውና ሁሉ የሚቀናብን ቤተሰቦች፤ በጭቅጭቅና ንትርክ ስማችን ደጅ ወጣ።

ነገሩ የሆነው እንዲህ ነው ትላለች ባለታሪካችን ወለተ ጊዮርጊስ፤ አንድ ቀን ታናሽ እህቴ ከተማውን መነጋገሪያ ካደረጉ አንድ "አጥማቂ ነኝ" ባይ ዘንድ ከጓደኛዋ ጋ እንደምትሄድ ራት ለመብላት በተሰበሰብንበት ትነግረናለች። ሁል ጊዜ ለኛ የሚጨነቀውና እንደ አባት የምናየው ታላቅ ወንድማችንን ለእኅታችን ጥያቄ የሚሰጠውን መልስ በጉጉት መስማት በመፈለጋችን አንዳችንም ከሱ ቀድመን ለእኅታችን መለስ ለመስጠት አልፈለግንምና ጸጥ ብለን መልሱን መጠበቅ ያዝን። ዘወትር ርጋታና አስተውሎት የማይለየው ወንድማችንም እንዲህ ሲል ሐሳቧን ተቃወመ፤ ጸበል መሄድ መልካም ነው። እውነት ነው መሄድም ይገባል። ነገር ግን እኔ ብትሄጂ ደስ የሚለኝ ጸበል ወዳለባቸው ገዳማት እና አብያተ ክርስቲያናት ነው። በዚያ ላይ ሱባኤም ይዘሽ በጽሙና ትጠበያለሽ፣ ጸሎትም ታደርጊያለሽ ይላል። ሁላችንም በወንድማችን ሐሳብ ተስማማን። ታናሽ እኅታችን ግን በፍጹም አለች፤ ይህኛው አጥማቂ እኮ ሸባ እየተረተሩ፣ እውር እያበሩና ካንሰር እያዳኑ ነው ብላ ተከራከረች። ብናስረዳትም ልታምን ወይም እኛን ልታሳምን አልቻለችም።ነገር ግን በሐሳብ ደርቃ ቀረች። ይሄን ጊዜ ወንድማችን ተዋት፣ እሷ ልጅ አይደለችም ሠርታ የምትገባና ራሷን ማስተዳደር የምትችል ሙሉ ሰው ናት ብሎ ያሰበችው እንዲሳካላት ሆነ።

ነገሩ የመጣው ከዚህ በኋላ ነው። እንደዚያ ተከራክራ የሄደችበት አጥማቂ ቤታችንን በጠበጠው፤ ያንን ሁሉ ፍቅር እንዳልነበር አደረገው። ልትጠመቅ የሄደችው እኅታችን ስትጠመቅ አጋንንቱ ከላይዋ ላይ ለፈለፈ ተባለ፤ ለፍልፎም ትዳር እንዳትይዝና ከቤት እንዳትወጣ፣ እጣ ፈንታዋ እንዳይገለጥ ታላቅ ወንድሟ አሠርቶባታል(ተብትቦባታል) ተባለ። በዚህ ጊዜ ሁላችን ወንድማችንን ጠረጠርነው፣ እንዳትሄድ ብሎ የተከራከረው ለካ ጉዱ እንዳይጋለጥ ነው ብለን ወንድማችንን መጣላት ጀመርን። በሰው ቢያስመክረን ንስሐ አባታችንን ቢልክ አንሰማህም አልነው።በዚህ ጊዜ ወንድማችን ቤት ተከራይቶ ከእኛ ወጥቶ ሄደ።በተለይ እኔ አሁን አሁን እውነታውን ለማመንም ላለማመነም ተቸግሪያለሁ። አንድ ጊዜ ያሳደገን ሕይወቱን ሙሉ ለኛ የከፈለው ወንድማችን እንዴት አጋንንት ይሄን አደረገ ስላለ ልክ ነው ብዬ ልቀበል ይላል፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሊያደርግ ይችላል ብሎ ይሞግተኛል።በርካታ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም ሆኑ መምህራን ስለነዚህ አሳቾች በዐውደ ምህረት አስተምረዋል፤ በመጻሕፍትም መስክረዋል። ሙሐዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በዚህ ጉዳይ ላይ ጥልቀት ያለው ጽሑፍ በብሎጋቸው አስነብበውን ነበር።

የዘመኑን "አጥማቂ" ነን ባዮች እውነተኞች ናቸው ብለን የማንቀበላቸው ምክንያቶች

እነዚህን አሳቾች "አጥማቂ" ናቸው ብለን የማንቀበልባቸው በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ ጸሐፊው በበርካታ አመክንዮ ያቀርባሉ፤ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ገዳማዊ ሕይወት፣ ክህነታዊ ሕይወት፣ የጸሎት ሕይወት ወይም ሌላ አንዳች ተጋድሎ ሳይኖረው

ማጥመቅ ብቻ ሥራው የነበረ ክርስቲያን የለም የሚሉት ሙሐዘ ጥበባት ሀብተ ፈውስ የተሰጣቸው አባቶችና እናቶች የሌላው መንፈሳዊ ሕይወታቸው ውጤት ወይም ነጸብራቅ ነበር እንጂ ሥራቸው እየዞሩ ማጥመቅ አልነበረም ይላሉ።

የሐዋርያት ሥራን ብናነብ ሐዋርያት ለወንጌል አገልግሎት ሲሠማሩ በአንድ በኩል አሕዛብን ወደ ክርስቶስ ለመጥራት በሌላ በኩል የአንደበት ትምህርታቸውን በእጃቸው ተአምር ለማጽናት ተአምራትን ያደርጉ ነበር እንጂ በአንድ ከተማ ውስጥ ሲያጠምቁ ውለው ያደሩበት፣ ወይም ከወንጌል አገልግሎት ተለይተው አጥማቂ ብቻ የሆኑበት፣ ወይም ደግሞ በዚህ ቦታ ፈውስ እንሰጣለንና ተሰብሰቡ ብለው ያስነገሩበት አንድም ማስረጃ የለም በማለት ይሞግታሉ። በገድለ ቅዱሳንም ቅዱሳን ጸጋ እግዚአብሔር ሲያድርባቸው፣ ሥጋቸውንና ሰይጣንን ድል ሲነሡ፣ በክርስትናቸው ሲበስሉ ተአምራት ይከተሏቸዋል እንጂ እንዲሁ ማጥመቅና መፈወስ ብቻ ሕይወቱ የነበረ ቅዱስ የለም ሲሉም ያስረዳሉ። ሰው ያለ ተጋድሎ እንዴት ጸጋ ያገኛል? ብለው የሚጠይቁት ሙሐዘ ጥበባት፤ በአሁኑ ዘመን ግን ከተራ ሰዎች የተለየ መንፈሳዊ ሕይወት የሌላቸው ሁሉ እየተነሡ አጥማቂ ሊሆኑ የቻሉበት አሳማኝ ምክንያት የለም በማለት ይሞግታሉ።

በቤተ ክርስቲያናችን ለመንፈሳዊ አገልግሎት በምንጠቀምበት በገድለ ቅዱሳን ውስጥ ቅዱሳን በገዳማዊ ሕይወት፣ በሰማዕትነት፣ በክህነታዊ አገልግሎት ሲሠማሩ እግዚአብሔር ምእመናንን ለመጥቀም ወይም ክብረ ቅዱሳንን ለመግለጥ በእነርሱ ላይ ተአምራትን ያደርጋል። እነርሱ ግን ይህ ክብር እንዳይገለጥባቸው ሲሸሹ፣ እኔ አላደረግኩም ሲሉ ወይም ስለራሳቸው ደካማነት ሲናገሩ እናያለን እንጂ ‹ኑ እንፈውሳችኋላን› ብለው ዐዋጅ ሲናገሩ አይተንም፣ አንብበንም አናውቅም። አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከአባ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ወጥተው ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም የሄዱበት ዋናው ምክንያት በገዳሙ እያሉ በፈወሱት አንድ በሽተኛ ምክንያት ስማቸው ከፍ በማለቱ፣ ብዙ ሰዎችም በመሰብሰባቸው የተነሣ ነው። ታላቁ አባት መቃርዮስ ገዳሙን ትቶ ወደ አንዲት መንደር መጥቶ የኖረው በገዳሙ ክብሩ በመገለጡና ተአምራት በመታየታቸው ከከንቱ ውዳሴ ለመሸሽ ነበር። ስምዖን ጫማ ሰፊው አካባቢውን ትቶ የጠፋው ተአምር አድራጊነቱ በመታወቁ ምክንያት ነበር። አሁን ግን ከዚህ በተቃራኒው ሰዎች እናጠምቃለን፣ እንፈውሳለን ብለው ማስታወቂያ የሚያስነግሩበት፣ ካሴት የሚሸጡበት፣ ፖስተር የሚሰቅሉበት ዘመን ነው።

ሙሐዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት አጥማቂያኑን አስመልክተው በጻፉት ሐተታ እንዳመለከቱት ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ ማን እንደሆነ፣ ድንግል ማርያም ማን እንደሆነች፣ ቅዱሳን መላእክት እነማን እንደሆኑ ሌሎቹም ቅዱሳን እነማን እንደሆኑ ጠንቅቃ ታውቃለች ታስተምራለችም ይላሉ። የእግዚአብሔርን ክብር ለሰዎች ሰጥታ አታውቅም ብለው ያስረዳሉ። ቅዱሳንን ከፈጣሪ አስበልጣ አታወቅም ይላሉ ጸሐፊው። የቅዱሳን መገኛና መሠረት በባሕርዩ ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር መሆኑን ታምናለች፣ ታስተምርማለች። ለእግዚአብሔር የማይቻል ለቅዱሳን ይቻላል፣ በእግዚአብሔር የማይሠራ በቅዱሳን ይሠራል ብላ አታምንም የሚሉት ጸሐፊው፣ እንዲህም ብላ አታስተምርም ይላሉ። በዘመኑ አጥማቂዎች ዘንድ የምናየው ግን ከዚህ በተቃራኒው ነው። በክርስቶስ ስም የማይወጣው ሰይጣን የቅዱስ ሚካኤልን ስም ሲጠሩበት ይወጣል። በክርስቶስ ስም የሚያሾፍ ሰይጣን የድንግል ማርያምን ስም ሲጠሩበት ተቃጠልኩ ይላል።ይኼ ፈጽሞ ክህደት ነው። የቤተ ክርስቲያንም ትምህርት አይደለም። ይላሉ አያይዘውም ‹‹በስመ ሥላሴ እቀጠቅጥ ከይሴ›› ብላ ያስተማረች ቤተ ክርስቲያን ላይ ‹‹በክርስቶስ ስም አንወጣም፣ በማርያም ስም ግን እንወጣለን›› እያለ አጋንንት ወጣ የሚል ትምህርት ማስፋፋት ክህደት እንደሆነ መእመናን ሊያውቁ እንደሚገባ ሊቃውንቱ በዘመናቱ ተናግረዋል፣ በቃል አስተምረዋል በመጽሐፍም ጽፈዋል በማለትም ያስረዳሉ።

# «አባቴ ከቤት ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን እስከምንደርስ ድረስ ያለማቋረጥ ውዳሴ ማርያም እየደገሙ ነበር የሚሄዱት፤»

በሚኒልክ ብርሃኑ

ክፍል ሁለት

***የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል።ቀጣዩን ክፍል ደግሞ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።***

**ስምዐ ጽድቅ፡- እስከ ዛሬ ምን ያህል ተማሪዎችን አስተምረዋል?**

**መምህር ኀሩይ ገ/ሥላሴ፡-** ከሰንበት ተማሪዎች እስከ መምህራን፣ ከአስኳላ ተማሪዎች እስከ ሠራተኞች ድረስ ብዙዎችን አስተምሬያለሁ። የማስተምረው በሁለት ፈረቃ ነው፤ ጠዋት ከ፫-፮ ሰዓት፣ ከሰዓት ፱-፲ ሰዓት። ይህ የሆነበት ምክንያት የአስኳላ ትምህርት በፈረቃ ስለነበር ጠዋት የሚገቡትን ከሰዓት፣ ከሰዓት የሚገቡት ደግሞ ጠዋት መጥተው እንዲማሩ ነው። ብዙ አገልጋይ ዲያቆናትንና ቀሳውስትን ማፍራት ችያለሁ። እኔ ዐቅም ኖሮኝ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። በቤተ ክርስቲያኑ ማስመስክር ስለሌለ እንጂ ብዙዎች ወደ መምህርነት ደረጃ የደረሱ አሉ፤ ያስመሰከሩም አሉ። በአሁኑ ጊዜ በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ማስመስከር እንዲቻል ተማሪዎቼ እንቅስቃሴ እያደረጉ ነው። ይህ ቢሳካ ደግሞ በአዲስ አበባ በርካታ ተተኪ መምህራን ማፍራት ይቻላል።

ከዚህ ባሻገር በማኅበረ ቅዱሳን ከ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ጀምሮ ኮቪድ-፲፱ እስከ ተከሠተበት እስከ ፳፻፲፪ ዓ.ም ድረስ ማታ ማታ አስተምር ነበር። በማኅበረ ቅዱሳን ትምህርቱ ሊጀመር የቻለበት ምክንያት መንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ እኔ ዘንድ መጥተው ይማሩ የነበሩ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ተመርቀው ሲወጡ ትምህርቱን አቋርጠውት ነበር። እነ ቀሲስ ያሬድ፣ ይልቃል የሚባሉ መጡና "ቀን በሥራ ምክንያት እርስዎ ዘንድ መጥተን መማር ስለማንችል፣ እንዲሁም ሌላ መምህር ከሚያስተምረን በለመድነው ጉረሮ ማኅበረ ቅዱሳን መጥተው ቢያስተምሩን" ብለው ጠየቁኝ። እኔም ቀድመውኑ የትምህርት ጉጉታቸውን አውቅ ስለነበር ተስማምተን ማስተማር ጀመርሁ። በዚህ መሠረት ያለማቋረጥ ለዐሥራ አራት ዓመታት በማኅበረ ቅዱሳን አስተምሬያለሁ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- በማኅበረ ቅዱሳን ምን ምን ነበር የሚያስተምሩት?**

**መምህር ኀሩይ፡-** መዝመረ ዳዊትን፣ ዜማን፣ ውዳሴ ማርያምን፣ ቅዳሴን፣ ሰዓታትን አስተምር ነበር።



መምህር ኀሩይ ገ/ሥላሴ

ቀደም ብዬ ተዘጋጅቼ፣ ለሠራተኞች በሚመች መልኩ ነበር የማስተምረው። በድምፅ እየቀዳሁ እሰጣቸውና

አጥንተው እንዲመጡ አደርጋለሁ። እነርሱም ጎበዞች ናቸው፣ አጥንተው መጥተው እኔ ጋር ይቀጽላሉ። የሰበሩትን፣ ያጣመሙትን እንዲያቃኑ አደርጋለሁ። የሚገርመው ደግሞ፣ በዚህ በማኅበረ ቅዱሳን ሳስተምር ሰዓታትን፣ ቅዳሴን ዘልቀው የነበሩ ሴቶችም ነበሩ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- እስከ አሁን ድረስ በዘለቀው የ፲፱ ዓመታት የማስተማር ጉዞ በርካታ ዲያቆናትን፣ ቀሳውስትን አፍርተዋል። እስካሁን ድረስ በምን በምን ዘርፍ አገልጋዮችን አብቅቼያለው ይላሉ?**

**መምህር ኀሩይ፡-** ብዙ ተማሪዎች ናቸው መጥተው የሚማሩት። ከደብሩ ጀምሮ በተለያየ ድርሻ የሚያገለግሉ ዲያቆናት፣ ቀሳውስት፣ የሰንበት ትምህርት ተማሪዎች አሉ፤ የደብሩ ስብከት ወንጌል ኃላፊዎችም እኔ ጋር መጥተው ይማራሉ። በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይኾን ከሀገር ውጪም ቅስና ተቀብለው የሚኖሩ በርካታ ተማሪዎች ነበሩኝ። ጀምረው ያቋረጡ በርካቶች ናቸው። ዲያቆናት እጅግ ብዙ ናቸው። ያስመሰከሩም አሉ። እኔ ዘንድ ተምረው የነበሩ በሕይወት የሌሉም ቄሶች አሉ። በሌላም ቤተ ክርስቲያን አስመስክረው በቅዳሴ መምህርነት የሚያስተምሩም፣ በዲቁና የሚያገለግሉም አሉ። በማኅበረ ቅዱሳን ከ፲፱፻፹፰ ዓ.ም ጀምሮ በኔ ወንበር የተማሩ በርካቶች ናቸው። ትምህርቱም የፈጸሙ፣ ያቋረጡም ብዙዎች ናቸው። በተለይ በማኅበረ ቅዱሳን የሚገኙ አገልጋዮች ከ፲፱፻፹፰ ዓ.ም ጀምሮ የእኔን ወንበር ያልጀመረ የለም ማለት ይቻላል። ትምህርቱን የፈጸሙም ብዙዎች ናቸው። የቅኔ መምህራችን የኔታ ፍስሓ "እስካሁን ምን ያህል ተማሪዎችን አስተማሩ" ተብለው ሲጠየቁ፤ "እግዚአብሔር ይቍጠራቸው እንጂ እኔ አላውቅም" ይሉ ነበር። እርሱ ይቍጠራቸው እንጂ በዚህ ሁሉ ዓመታት እስካሁን ድረስ የተማሩትን እኔም አላውቃቸውም። ግን ብዙ ቦታ እያገለገሉ ያሉ፣ መንገድ ላይ ሲያገኙኝ "የኔታ አስታወሱኝ የእርስዎ ተማሪ ነበርሁኝ" የሚሉኝ በርካታ ናቸው። በውጪም፣ በሀገር ውስጥም የሚኖሩ ብዙዎች እየመጡ ይጠይቁኛል። እግዚአብሔር ይመስገን እርሱ ፈቅዶ ብዙዎችን አፍርቻለሁ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- በአሁኑ ጊዜ ምን ያህል ተማሪዎችን እያስተማሩ ነው?**

**መምህር ኀሩይ፡-** በአሁኑ ጊዜም ያሉ ተማሪዎች ብዙ ናቸው። የአስኳላ ተማሪዎች፣ ሰንበት ተማሪዎች፣ ሠራተኞችም፣ መምህራን፣ ክረምት ክረምት መጥተው የሚማሩም፣ በተለያዩ ቤተ ክርስቲያናት በዲቁና፣ በቅስና፣ በሌላም በሌላም እያገለገሉ የሚገኙ ተማሪዎች አሉ። ባጠቃላይ ከሠላሳ በላይ ይሆናሉ። የአስኳላ ትምህርት ስለተጀመረ ወደዚያ የሔዱ ስላሉ አሁን ቍጥሩ ቀንሷል። በቅርቡ መዝገበ ቅዳሴን የዘለቁ፣ ወደ ደብረ ዓባይ ሔደው አስመስክረው ለመምጣት የተዘጋጁ ተማሪዎች አሉኝ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- አባታችን ከልጅነት እስከ ዕውቀት ዘመን የዘለቀው የትምህርት ሒደት እንዲሁ በቀላሉ አልጋ ባልጋ አይሆንምና ያጋጠሞት መልካምም ሆነ መጥፎ አጋጣሚ ካለ ቢያጫውቱን?**

**መምህር ኀሩይ፡-** እውነት ነው! ሁሉም ነገር አልጋ ባልጋ አይሆንም። የማስታውሰው አዲግራት ደብረ መዓር የሚባል ቦታ ከየኔታ ንጉሥ ዘንድ ቅኔ በምማርበት ጊዜ አካባቢው ለልመና የማይመች በመሆኑ አንዳንድ ጊዜ ስንቅ ያልቅ ነበር። ስንቅ ሲያልቅ ጾም ማደር አለ፤ ሳይጠግቡና ሳይቀምሱም ማደርም አለ፤ ሳይደሰቱ ማደር አለ። ትንፋሽ ማሳደሪያ ትንሽ ቍራሽ ከተገኘ ግን ብዙ አንጨናነቅም። ይህ ሁሉ ቢሆንም መራባችንና መጠማታችን ብዙም አያሳስበንም። ምክንያቱም ትኩረታችን ትምህርቱ ላይ ነበር። ምን እበላለሁ? ምንስ እጠጣለሁ? የሚለው አሳብ አስጨናቂ አልነበረም። ግን ብዙ ውጣ ውረድ ነበረው። በሐውዜን ከየኔታ ሐረገ ወይን ዘንድ ያጋመስሁትን ሰዓታትና የውዳሴ ማርያም ዜማን ስማር መምህሬም፣ የአካባቢው ማኅበረሰብም ይወዱኝ ስለነበር ብዙም አልተቸገርሁም። ከዚያ ተመልሼ ቅኔን ለማብሰል ወደ የኔታ ፍስሓ ስሔድ ግን በተለየ ሁኔታ ችግር ገጥሞኝ ነበር። በእርግጥ ችግሩ በእኔ ላይ ወይም እኔ በምማርበት አካባቢ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በሰሜን የተከሠተው የ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ረኀብ ነበር። ይህ ወቅት በጣም ፈታኝ ጊዜ ነበር። የረኀቡን ጊዜ ለማሳለፍ መምህራን ወንበራቸውን ያጠፉበት፣ ተማሪዎችም የተበተኑበት ጊዜ ነበርና መምህራችን የኔታ ፍስሓ ርዳታ ለመጠየቅ ወደ መቐሌ መጥተው ነበር። በኋላ በጣም ቆዩብን፤ እኛም ተቸገርን፣ ረኀቡም ጠናብን፤ ወደየመጣንበት ተበተንን። እኔም ወደ ቤተሰቦቼ ተመልሼ ሄድሁ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- የረኀብ ዘመኑ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያደረሰው ተጽእኖ ምንድን ነበር?**

**መምህር ኀሩይ ገ/ሥላሴ፡-** በነበርሁበት በአዲግራት ደብረ ጽጌ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ተስተጓጉሎ ነበር። ወደ ስደትም የሄዱ አገልጋዮች ነበሩ። እሑድ እሑድና የገብረ መንፈስ ቅዱስ ዕለት ነበር የሚቀደሰው። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ክርስትናና ፍትሐት ካለ አገልግሎት ይሰጣል። ሁለት ቀዳሾች ነበርን ያለነው። ሕዝቡም በሚገርም ሁኔታ ለቤተ ክርስቲያን ያደላ ነበር። ዐቅም ያላቸው የተቻላቸውን ይሰጡ ነበር። እኔም ትምህርቱን ለአንድ ዓመት አቋርጬ የረኀብ ዓመቱ ሲያልፍ እንደገና በዓመቱ በ፲፱፻፸፰ ዓ.ም ተመልሼ መጣሁና ቅኔዬን ጨረስኩ።

ሌላው ብዙም ባይባል፣ ፈታኝ አጋጣሚ የምለው በማኅበረ ቅዱሳን በማስተምርበት ወቅት ነበር። ቀን መንበረ ልዑል ሳስተምር እውልና ይደክመኛል። ዕረፍት ለማድረግ

ብየ ለመቅረት በምፈልግበት ጊዜ እኔን ብለው ከሥራ ውለው ማታ የሚመጡ ተማሪዎቼን ሳስብ ያሳዝኑኛል፤ እየደከመኝም ቢሆን እመጣ ነበር። የማስተምርበትም ሰዓት ማታ ከ፪-፬ ሰዓት ስለነበር ለእኔ ከብዶኝ። አምሽቼ ነበር የምወጣው። ለተወሰነ ጊዜ ተፈትኜ ነበር። ነገር ግን ፈተና በዓለም ላይ ስንኖር ግድ ነውና ፈተናው አይቀርም። በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በእመቤታችን ርዳታ ፈተናውን አልፌዋለሁ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- በቤተ ክርስቲያን ያለውን አገልግሎት ማስተማር ብቻ አይደለምና የመቅደሱን አገልግሎት ከማስተማሩ ጋር እንዴት አቻችለው አስሄዱት?**

***መምህር ኀሩይ፡-*** የአብነት ትምህርት መርሐ ግብሩ ዓመቱን ሙሉ ሲቀጥል በዓመት ሁለት ጊዜ በሕማማትና ፍልሰታ ወንበሩ ይነሣል። በሕማማት የቤተ መቅደስ አገልግሎቱ እስከ ምሽቱ ዐሥራ አንድ ሰዓት ስለሆነ ወንበር ዘርግቶ ለማስተማር ይከብዳል። በፍልሰታ እንዲሁ የማስተምርበት መጠለያ ምእመናን ለሱባዔ ስለሚይዙት ትምህርት አይሰጥም። በቤተ መቅደስ አገልግሎት በአርባ ጾም ስብሐተ ነግህ ከሌሎች አገልጋይ ወንድሞቼ ጋር እንቆማለሁ። ሰዓታትም እንዲሁ በፈቃደኝነት እቆማለሁ። ስብሐተ ነግህ ከ፲ ሰዓት ጀምረን እስከ ኪዳን እንጨርሳለን። ከዚያ በኋላ እስከ ፫ ሰዓት ጸሎቴን አደርሰለሁ። ልክ ፫ ሰዓት ሲል ወደ ወንበሬ እሄድና ቅዳሴ እስከመግቢያው ድረስ አስተምራለሁ።

ከቅዳሴ በኋላ ከ፱-፲፪ በድጋሜ አስተምራለሁ። ከተጉና እግዚአብሔር ከፈቀደ ሁሉንም ነገር ማሟላት ይቻላልና በተቻለኝ መጠን የምችለውን አገልግሎት ሁሉ እፈጽማለሁ። ሌላው የፍትሐት ተረኛ በምሆንት ጊዜ በቅድሚያ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎት ነው የማደላው። ማስተማር የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አይደለም እያልሁ ሳይሆን ተማሪዎች እርስ በርሳቸው መማማር እንዲችሉ አደርግና ወደ አገልግሎቱ እሄዳለው ማለት ነው። እሑድ እሑድ፣ እንዲሁም የቅዱስ ማርቆስና የቅዱስ ሚካኤል ዕለት ማኅሌት እንቆማለሁ። በአጠቃላይ ሁሉንም የዐቅሜን ደርቤ አገለግላለሁ ብዙም አላስቸገረኝም።

**ስምዐ ጽድቅ፡- የአብነት ትምህርት ቤቶች በብዛት የሚገኙት ከከተማ ወጣ ባሉ አካባቢዎች ነው። እንደ አዲስ አበባ ባሉ ከተሞች ውስጥ የሚገኙት ደግሞ በጣት የሚቈጠሩ ናቸው። የአብነት ትምህርት ቤቶች በከተማ ላይ እንዲስፋፉ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

***መምህር ኀሩይ፡-*** በአዲስ አበባ የአብነት ትምህርት ቤቶች እንዲስፋፉ ሀገረ ስብከቱም ይሁን ቤተ ክህነት መከታተል አለበት። ምእመናንም በተለየ መልኩ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው። አብነት ትምህርት ቤቶች ከፍተኛ ትኩረት ይፈልጋሉ። ምክንያቱም እነርሱ ከሌሉ በቤተ ክርስቲያን ያለው አገልግሎት እጅግ ይጎዳል። ምክንያቱም የአብነት ትምህርት ቤት ለቤተ ክርስቲያን የጀርባ አጥንቷ ነውና። ሁሉም ከአብነት ትምህርት ቤት ወጥቶ ነው ቤተ ክርስቲያንን እያገለገለ ያለው። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በስፋት እንዲካሄድ የአብነት ትምህርት ቤቶች ትኩረት ያስፈልጋቸዋል። ወደ ከተማዋ የሚመጡትም ይሁኑ፣ የከተማዋ ምእመናን ወደ ዘመናዊ ስለሚያደሉ እንጂ መምህራን ጠፍተው አይደለም፤ በየቤተ ክርስቲያኑ ሞልተዋል። ግን ሳይቸገሩ እንዲያስተምሩ ምቹ ሁኔታ ቢፈጠርላቸው፣ ከተሜዎቹ የአብነት ተማሪዎች እንደገጠሩ ‹‹በእንተ ስማ ለማርያም›› ብለው እየለመኑ መማር ስለማይችሉ ልክ እንደ ታዕካ ነገሥትና ምስካየ ኅዙናን በስፋት በመገንባት፣ በቀንም በአዳርም ትምህርት እንዲሰጥ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ይገባል። እንደዚህ ሲሆን ተማሪዎች ይማራሉ፤ አብነቱም ይስፋፋል።

**ስምዐ ጽድቅ፡- አባታችን ጥያቄያችንን ጨርሰናል በስተመጨረሻ ቀረ የሚሉት ነገር ነገር ካለ?**

***መምህር ኀሩይ፡-*** ሁል ጊዜ ከአእምሮዬ የማይጠፋ፣ ሁል ጊዜም ቢሆን የማስበው አንድ ነገር አለ፤ ከአባቴ ጋር ዘወትር ቤተ ክርስቲያን በሌሊት እንሄዳለን። ቤተ ክርስቲያኑ ያለው ተራራ ላይ በመሆኑ ከቤታችን ይርቃል። እርሳቸው ከፊት እኔ ከኋላ እየተከተልኩ ግማሹን እርሳቸው ቀሪውን ደግሞ እኔ መጽሐፍ ተሸክመን አብረን እንሄድ ነበረ። በዚያ ሁሉ ዓመታትው ውስጥ ግን አንድ ቀን እንኳን እንከን አጋጥሞን፣ አውሬም አስደንግጦን፣ እንቅፋትም መትቶን አያውቅም።

በሰላም እንደወጣን በሰላም ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እንደርስ ነበር።አባቴ ከቤት ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን እስከምንደርስ ድረስ ያለማቋረጥ ውዳሴ ማርያም እየደገሙ ነበር የሚሄዱት፤ መለስ ብለው እኔንም “አትደግምም?” ይሉኝ ነበር።ይህንን ነገር ሁል ጊዜ ነው የማነሣው፣ የእግዚአብሔርን ጥበቃውን ሳስብ ሁል ጊዜም ይገርመኛል።አባቴ ለዚህ እንድበቃ በጣም ተግተዋል፣ ደክመዋልና አመሰግናቸዋለሁ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- አባታችን ለነበርን ቆይታ በእግዚአብሔር ስም እናመሰግንዎታለን።**

***መምህር ኀሩይ፡-*** እናንተም እኔን አክብራችሁ ለመጠየቅ እዚህ ድረስ ስለመጣችሁ እግዚአብሔር ይስጥልኝ፤ አመሰግናለሁ።

# “ከላይ እስከታች ያሉ የመንግሥት አካላት ለተሰየሙበት ሥልጣንና ለሚያገለግሉት ሕዝብ ታማኝ መሆን አለባቸው”





ድብደባ የተፈጸመባቸው መ/ር ገዛኸኝ አበራና የጦቂሳ ጎዶ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን

*በካሣሁን ለምለሙ*

የስደት ዘመኗ የማያበቃው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዛሬም እንደትናንቱ ስደቷ በዝቶ መገፋቷ በርትቶ ማየት የዘወትር ተግባር እየሆነ መጥቷል:: ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በደልና መገፋት የሚደርስባት ሕዝብና መንግሥት የሰጣቸውን ኃላፊነት ወደጎን በተውና የራሳቸውን ሃይማኖት ተቋም የጠቀሙ በሚመስላቸው የታችኛው የመንግሥት ባለሥልጣናት አማካይነት ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ በሃይማኖት አክራሪነት የተጠመዱ እኩያን ናቸው:: እነዚህ የእኩይ ተግባር ሰለባዎች ተጣምረው ላለፉት በርካታ ዓመታት በተለይም ላለፉት ተከታታይ ሦስት ዓመታት በቤተ ክርስቲያን ላይ ያለከልካይ ከፍተኛ በደል ፈጽመዋል::

ኦርቶዶክሳውያንን ማሳደድ፣ መግደል፣ ንብረታቸውን መዝረፍ፣ የማምለኪያ ቦታቸውን ማውደምና ማቃጠል እንዲሁም የዐደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎችን በመንጠቅ ጭምር ለሌላ አገልግሎት ማዋል ዋና ዋና የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች እያከናወኑት ያለ እኩይ ተግባር ነው:: የቤተ ክርስቲያኗ መገለጫ የሆኑ የዐደባባይ በዓላትን ለማደብዘዝ ብሎም ለማጥፋት የበዓላት ማክበሪያ ይዞታዎችን ይነጥቃሉ፤ በበዓላት ወቅትም ምእመናንን የማዋከብ ድርጊት ይፈጽማሉ:: ተግባሩ በኦሮሚያና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች በተደጋጋሚ የሚስተዋል ሲሆን አባቶችን አሳዝኗል ምእመናንንም አስከፍቷል::

በወላይታ ዞን አንዳንድ የመንግሥት ባለሥልጣናት ቤተ ክርስቲያንን ለበርካታ ዘመናት ሲያሳድዷትና ሲበድሏት መቆየታቸው ያንገበገባቸው አገልጋይ አባቶችና ምእመናን ባደረጉት መራራ የፍትሕ ትግል ጉዳዩ ከከፍተኛ የዞኑ አመራሮች ደርሶ አመራሮቹም ችግሩን እንደሚፈቱና በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚፈጸምን በደልና ኢፍትሐዊ ድርጊት ለማስቆም በትኩረት እንደሚሠሩ ማስታወቃቸውን ከዚህ ቀደም ከሀገረ ስብከቱ አባቶች ያገኘነውን መረጃ ዋቢ አድርገን ዘግበናል:: በወቅቱም በሕገ ወጥ መንገድ የተነጠቁ ሕጋዊ የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎች ሁሉ እንደሚመለሱ ቃል መግባታቸውን አስነብበናል:: ይሁን እንጅ ካሳለፍነው ሐምሌ ፳፫ ቀን ፳፻፲፫ዓ/ም ጀምሮ በወላይታ ሀገረ ስብከት በቦኖስ ሶሬ ወረዳ ጦቂሳ ጎዶ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ይዞታዎች ላይ በአካባቢው የመንግሥት ባለሥልጣናት አማካይነት ከፍተኛ በደል እየተፈጸመ መሆኑን ከአካባቢው አባቶች ከተገኘው መረጃ ለመረዳት ችለናል:: አባቶች መደብደባቸውንና መዋከባቸውን

እንዲሁም በመስቀልና በጥምቀት በዓላት ማክበሪያ ቦታዎች ተተክለው የነበሩ ዐጸዶች ሁሉ መውደማቸውን የጦቂሳ ጎዶ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ዋና አስተዳደሪ የሆኑት መምህር ገዛኸኝ ዴንሳ ጋር በስልክ በነበረን አጭር ቆይታ ነግረውናል፡፡ ከእሳቸው ጋር ያደረግነውን ሙሉ ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በጦቂሳ ጎዶ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን የተፈጠረ ነገር ምንድን ነው?**

**መ/ር ገዛኸኝ ዴንሳ፡-** በወላይታ ሀገረ ስብከት በቦናስ ሶሬ ወረዳ ቤተ ክህነት የጦቂሳ ጎዶ ቅድስት ኪዳነምሕረት ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፺፪ ዓ.ም የተመሰረች ሲሆን የተሟላ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ባለቤትም ናት፡፡ ይህ ሆኖ እያለ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ መንግሥት ያወጀውን የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብርን ለመተግበር ምእመናንና አገልጋዮችን አስተባብራ የችግኝ ተከላ ሥራዎችን በምትሠራበት ወቅት ሐምሌ ፳፫ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም የአካባቢው የመንግሥት ባለሥልጣናት በምእመናንና በእኛ አገልጋዮች ላይ ከፍተኛ እንግልትና ወከባ አድርሰዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያንን ሕጋዊ ይዞታዎችን ለመንጠቅ ባለመ ሁኔታ የተተከሉ ችግኞችን ከመንቀል በተጨማሪ በእኔንና በሌሎች አገልጋዮች ላይ ከፍተኛ የሆነ ድብደባ በመፈጸም ለእስር ዳርገውናል፡፡

በእኔ ላይ ባደረሱብኝ ከፍተኛ የሆነ አካላዊ ድብደባ ለከፍተኛ የጤና እክል ተዳርጌ በሕክምና ስረዳ ቆይቼ መጠነኛ የጤና መሻሻል አግኝቻለሁ፡፡ በእኔ ላይ ከደረሰው መከራ በተጨማሪ ከዐሥራ አንድ በላይ የሰንበት ተማሪዎች ከፍተኛ ድብደባና ወከባ ተፈጽሞባቸዋል፡፡ ለቤተ ክርስቲያን ምንም ዓይነት ክብር ሳይሰጡ ቅጥሯ ድረስ ዘልቀው ይህንን ያህል ግፍ በሁላችን ላይ ፈጽመዋል፡፡ እንደሚታወቀው የሰው ልጅ በሕግ ጥላ ሥር ከዋለ በኋላ በሕግ አግባብ ይጠየቃል እንጂ ድብደባና እንግልት አይፈጸምበትም፡፡ እኛ ግን ያልጥፋታችን በሕግ ቁጥጥር ሥር ከዋልን ዕለት ጀምሮ ከፍተኛ የሆነ እንግልትና ድብደባ ሲፈጸምብን ቆይቷል፡፡

ለተወሰነ ቀናት ታስረን ከተለቀቅን በኋላም ወደ መደበኛ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዳንመለስ ከፍተኛ የሆነ የደኅንነት ሥጋት ፈጥረውብናል፡፡ እየተፈጸመብን ያለው ግፍ ከአእምሮ በላይ ስለሆነና የቅርብ አጋዥ ባለማግኘታችን በመላው ዓለም ያሉ ምእመናን ድምጻችንን ሊያሰሙልን ይገባል፡፡ የአካባቢው የመንግሥት ባለሥልጣናት ሃይማኖትን ከሃይማኖት ለማጋጨት ጥረት እያደረጉ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን "ከአካባቢው ካልጠፋች" ደስታ እንደማያገኙ በተደጋጋሚ ገልጠዋል፡፡ ችግሩ በሰላምና በሕግ አግባብ ብቻ እንዲፈታ እኛም ሆን የወላይታ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ክቡር መልአከ ሰላም ቦኪቻ ኢንጋ ጥረት እያደረግን እንገኛለን፡፡ የቤተ ክርስቲያን ሕጋዊና ነባር ይዞታዎች ለሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ በሕግ አግባብ የፍርድ ቤት ክርክር እያደረግን እንገኛለን፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በእርስዎና በሌሎች ላይ ድብደባና እንግልት የፈጸሙ የፀጥታ አካላት ላይ የተወሰደ ርምጃ ምንድን ነው? ችግሩን ለመፍታትስ ምን እየሠራ ነው?**

**መ/ር ገዛኸኝ፡-** ወንጀሉን የፈጸሙት አካላት በማን አለብኝነት የተነሡ በመሆኑና ጉዳዩም በክስ ይፈታል ብለን ባለማመናችን የሚመጣውን ችግር ሁሉ በትዕግሥት እየተጋፈጥን እንገኛለን፡፡ በመሆኑም እስካሁን ድረስ ችግር በፈጠሩት አካላት ላይ የተወሰደ ምንም አይነት ርምጃ የለም፡፡ ፍርድን ከፈጣሪ በመጠበቅ የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዞታ ለማስከበር ግን ፍርድ ቤት ድረስ ሄደን ለበርካታ ዙር ክርክር እያካሄድን እንገኛለን፡፡ ወንጀለኛ የአካባቢው የፀጥታ ኃይሎችንና ካድሬዎችን እንዳንከሳቸው ‹‹ልጁ ቀማኛ አባቱ ዳኛ›› ዓይነት በመሆኑ ያን ያህል ርቀት አልተጓዝንም፡፡ እግዚአብሔር ከረዳንና የተሻለ ጊዜ የሚመጣ ከሆነ ሁሉም ከሕግ በታች የሚሆኑበትን ሥራ እንሠራለን፡፡ ለጊዜው ግን ሕጋዊ የሆነችው ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን መብቷንንና ክብሯን እንዲሁም ይዞታዎቿን በማስጠበቅ ላይ ብቻ ትኩረት አድርገን በመሥራት ላይ እንገኛለን፡፡

የዐደባባይ በዓላትን ጭምር በቤተ ክርስቲያኗ ሕጋዊ ይዞታ ላይ እንዳይከበር የተከለከልን ቢሆንም ጉዳዩን በትዕግሥት በማለፍ ነገሮችን በሕግና በውይይት ለመፍታት ጥረት እያደረግን እንገኛለን፡፡ ለወደፊትም ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን የራሳቸውን ድርሻ በመውሰድ ችግሩን በአጭር ጊዜ ለመፍታት ርብርብ ይደረጋል ብዬ አምናለሁ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በቤተ ክርስቲያኗ ላይ እየተፈጸመ ያለው ጥፋት ሃይማኖታዊ ነው ብሎ ያምናኑሉ?**

**መ/ር ገዛኸኝ፡-** ጥቃቱ ሃይማኖታዊ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ የአካባቢው የመንግሥት ባለሥልጣናት የተዛነፈ ሕግና መመሪያን ሽፋን አድርገው ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ጥረት እያደረጉ ነው፡፡ አንዳንዶች የወቅቱን የሀገሪቱን የፖለቲካ ያለመረጋጋት እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ‹‹ቤተ ክርስቲያንን ካላጠፋን ዕረፍት አናገኝም›› በማለት የሚዝቱትን በተግባር እየገለጡ ይገኛሉ፡፡

በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት እኛ አገልጋዮች ሆነ ምእመናን ከመንግሥትና ከማኅበራዊ አገልግሎት እንድንታገድ ሆነናል፡፡ ይሁን እንጂ የሀገረ ስብከቱ ሥራ

አስኪያጅ እየተፈጸመ ያለውን ችግር ሃይማኖታዊና ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት እንደሆነ በማወቃቸው አስፈላጊ ያሉትን ሁሉ እንደሚያደርጉ ከመናገራቸው በተጨማሪ በማግሥቱ በአካባቢው ተገኝተው የማጽናናት ሥራ ሠርተዋል። ስላደረጉት ነገርም እኛ እናመሰግናቸዋለን።

**ስምዐ ጽድቅ፡- ችግሩን ለመፍታት በሀገረ ስብከቱ በኩል ምን ዓይነት እገዛ እየተደረገላችሁ ነው?**

**መ/ር ገዛኸኝ፡-** ሀገረ ስብከቱ በሥራ አስኪያጁ በኩል በጋራ ችግሩን ለመፍታት ጥረት እያደረገ ነው። በሂደቱ ላይ የወላይታ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ መልአከ ሰላም ቦኪቻ ኢንጋ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ። በጉዳዩ ዙሪያ ፍርድ ቤት ላይ በምናደርገው ክርክር ከፍተኛ እገዛ እያደረጉልን ነው። ምእመናንና እኛ አገልጋዮች ያለንን የግል ንብረት ሁሉ ሸጠንም ቢሆን በቀጣይ የቤተ ክርስቲያን ይዞታ ለማስከበር ጥረት እናደርጋለን። ምንም እንኳን ቤተ ክርስቲያኗ የራሷ የሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ቢኖራትም ማስረጃውን ከማስረጃነት ያልቆጠሩ ጥቂት የአካባቢው የመንግሥት ባለሥልጣናት ቤተ ክርስቲያን እንድትፈርስ እና የጥምቀትና የመስቀል በዓላት ማክበሪያ ቦታዋን ለመንጠቅ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- ለሃይማኖታቸውና ለቤተ ክርስቲያናቸው ብለው እንደእርስዎ ዋጋ ከከፈሉ አባቶች ሌሎች ምን ይማራሉ?**

**መ/ር ገዛኸኝ፡-** አባቶችም ሆኑ ምእመናን ማዕተባቸውን ማጥበቅ እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያናቸው መክፈል ያለበትን ሁሉ ዋጋ መክፈል ይጠበቅባቸዋል። በሃማኖታችንና በቤተ ክርስቲያናችን የሚመጣውን ፈተና ሁሉ ያለምንም ፍርሃትና መሸማቀቅ መመከት አለብን። ለሃይማኖት ብሎ ዋጋ መክፈል ሰማያዊ ዋጋ እንደሚያስገኝ መዘንጋት የለብንም። እኔም በሕይወት እስካለሁ ደረስ ቤተ ክርስቲያኔን በቅዳሴ፣ በመዝሙር እንዲሁም በትምህርትና በሌሎች ጉዳዮች ላይ በሙሉ አቅሜ አገልግሎት እሰጣለሁ። ለሕይወቴ የማልሳሳ በመሆኔም ሀብት ንብረቴን፣ ልጆቼንና ቤተሰቦቼን እንዲሁም ኑሮዬን ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቻለሁ። የእኔና የቤተሰቤ ክብር ከቤተ ክርስቲያን ክብር ብታች ነውና።

**ስምዐ ጽድቅ፡- አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያንን ችግር ለመፍታት ከቤተ ክርስቲያን ምን ይጠበቃል ይላሉ?**

**መ/ር ገዛኸኝ፡-** በየጊዜው እዚያም እዚህ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት የመጀመሪያው ርምጃ አባቶቻችን ጠንካሮችና የውሳኔ ሰዎች መሆን አለባቸው። ሰንበት ትምህርት ቤቶችም የልጅነት ድርሻቸውን በተገቢ መንገድ መወጣት አለባቸው። መምህራንም ሆኑ አባቶች ምእመናን ሃይማኖታቸውን ጠንቅቀው አውቀው ለቤተ ክርስቲያናቸው ዘብ እንዲቆሙ ማድረግ ያስፈልጋል፤ የቤተ ክርስቲያንን ክብርና መብት የሚያስጠብቁ እንዲሆኑም በደንብ መቅረጽ ያስፈልጋል እላለሁ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- በተደጋጋሚ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደርሰውን ችግር ለመፍታት ከመንግሥት አካላት ምን ይጠበቃል?**

**መ/ር ገዛኸኝ፡-** መንግሥት በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት በሚደረግ ጥረት ላይ ከፍተኛ ኃላፊነት አለበት። በተለይ ለሀገር ዋስና ጠበቃ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ክብርና መብት መጠበቅ የመንግሥት ዋነኛ ድርሻ ሊሆን ይገባል። ከላይ እስከታች ያሉ የመንግሥት አካላት ለተሰየሙበት ሥልጣንና ለሚያገለግሉት ሕዝብ ታማኝ መሆን አለባቸው። ቤተ ክርስቲያን ለሀገርና ለወገን ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረከተች መሆኗን በመገንዘብ መንግሥት መብትና ክብሯን ሊጠብቅ ይገባል።

**ስምዐ ጽድቅ፡- ቀረ የሚሉት ነገር ካለ?**

**መ/ር ገዛኸኝ፡-** እኔ የማስተዳድራት የጦቂሳ ጎዶ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን በዘመን ብዛት የመፍረስ አደጋ እየገጠማት እና በቂ ንዋየ ቅድሳትና ልብሰ ተክህኖ ስለሌላት የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ያገባኛል የሚል ሁሉ እጁን እንዲዘረጋ እማጸናለሁ። አገልጋዮቿም ያለምንም ደመወዝ ለበረከት ብለው የሚያገለግሉባት አጥቢያ ናት።

በቅርቡ የገጠመንን ፈተና በተባበረ ኃይል ነውና የሚታለፈው ሁሉም አገልጋይም ሆነ ምእመን የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪ አቀርባለሁ። በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያንን መብትና ክብር ማስከበር ለነገ የማይባል ተግባር ሊሆን ይገባል። በቀደሙ አባቶቻችን መሥዋዕትነትና ተጋድሎ እዚህ የደረሰችን ቤተ ክርስቲያን ክብሯን ባለማስደፈር ከነማንነቷ ጠብቀን ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ የልጅነት ግዴታችን ነው።

# የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ታሪክ ለልጆች፤

በምኒልክ ብርሃኑ

ልጆች እንደምን ከረማችሁ! እግዚአብሔር ይመስገን እኛ በጣም ደኅና ነው። በዛሬ ቆይታችን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ ካደረጉ ቅዱሳን አባቶች መካከል ቀዳሚ ስለኾነው ሐዋርያ እንማራለን።

ልጆች! ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ፴፬ ዓ.ም. ነው። የገባውም በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ቅዱስ ባኮስ አማካይነት ነው። በመሆኑም ክርስትና እንዴት ወደ ሀገራችን እንደገባ፣ ቅዱስ ባኮስ ለቤተ ክርስቲያናችን ምን አስተዋጽኦ እንዳደረገ በደንብ እንማራለን፤ አብራችሁን ቆዩ።

ልጆች! ሀገራችን ኢትዮጵያ ክርስትናን ከመቀበሏ አስቀድሞ በንግሥት ሳባ አማካይነት የእግዚአብሔርን ታመልክ ነበር። የሳባ ንግሥት የእስራኤል ንጉሥ የነበረው ጠቢቡ ሰሎሞን ዝናውን እና ጥበቡን ሰምታ ልትጎበኘው ሄደች።(፩ኛዜና መዋዕል ፱፥፩) ታዲያ ይቺ ንግሥት ወደ ንጉሥ ሰሎሞን በሄደች ጊዜ ከንጉሡ ፀነሰች። ምኒልክ የሚባልም ልጅ ወለደች።

ንጉሥ ሰሎሞንም ለንግሥት ሳባ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ በኢየሩሳሌም ቦታ ሰጣት። በዚህም ቦታ የሚያምር ቤተ መቅደስ አሠራች። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያውያን በየዓመቱ ወደ ኢየሩሳሌም እየመጡ በቤተ መቅደሱ እየተሳለሙ ሥርዓተ አምልኮን ይፈጽሙ ጀመር።


ልጆች! ከብዙ ጊዜ በኋላ ሕንደኬ የምትባል ንግሥት በኢትዮጵያ ነገሠች። ታዲያ ይቺህ ንግሥት የቀደመውን የአባቶቻችንን ሥርዓት ለመፈጸም ባኮስ የሚባለውን ጃንደረባ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄድ አዘዘችው። እርሱም ኢየሩሳሌም በሚገኘው የኢትዮጵያ ቤተ መቅደስ ሊሳለም፣ ሊሰግድ እና ከንግሥት ሕደንኬ የተላኩትን የተለያዩ ስጦታዎች ለቤተ ክርስቲያኗ ሊያስረክብ በሠረገላ ጉዞውን ጀመረ።

ልጆች! ‹‹ጃንደረባ›› ማለት የቤተ መንግሥት ንብረት ጠባቂ፣ የንግሥት ወይም የንጉሥ ታማኝ አገልጋይ ማለት ነው። ሠረገላ ደግሞ በዱሮ ጊዜ ከእንጨትና ከብረት በተሠራ ጋሪ በፈረስና በበቅሎ የሚጎተት ለመጓጓዣ የሚያገለግል መሣርያ ነው። ታዲያ ጃደረባው ባኮስ በዚህ ሠረገላ ላይ እየተጓዘ .... እየተጓዘ .... ከብዙ ልፋት እና ድካም በኋላ ኢየሩሳሌም ደርሰ። ወደ ቤተ መቅደሱም ሔዶ ሥርዐተ አምልኮን ፈጸመ። ከዚያም ከንግሥቲቷ የተላኩትን ስጦታዎች አስረከበ። በመጨረሻም ወደ ሀገሩ ለመመለስ እንደገና በሠረገላ ላይ መንገዱን ጀመረ።

ታዲያ ልጆች! ጃንደረባው ባኮስ በዚህ ሠረገላ ላይ ሆኖ መጽሐፍ ቅዱስ እያነበበ ይጓዝ ነበር። እናንተስ በታክሲ ወደ ተለያየ ቦታ ስትሔዱ መጽሐፋችሁን ወይም ደብተራችሁን ታነባላችሁ? አያችሁ ልጆች! ባኮስ ግን በመንገድ ሳለ መጽሐፍ ያነብ ነበር። እናንተም እንደ ባኮስ ማንበብ አለባችሁ። ጃንደረባው ባኮስ መጽሐፍ ቅዱስን እያነበበ ሳለ ጋዛ የሚባል ቦታ ደረሰ።ነገር ግን የሚያነበው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በደንብ ሊረዳው አልቻለም።

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያስተምረውና የሚያስረዳው ሰው ይፈልግ ነበር። በዚህ ጊዜ ቅዱስ ፊልጶስ የተባለ ሐዋርያ ሊያስተምረው ከእግዚአብሔር ተልኮ ወደ ባኮስ መጣ። ወደ ሠረገላውም ቀረብ ብሎ "በውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህን?" አለው ፤ እርሱም "የተረጉመልኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል?"

ብሎ መለሰለት። ከዚያም ሐዋርያው ፊልጶስ ባኮስን ሊያስተምረው ሠረገላው ላይ ወጣ።



*ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ ጃንደረባ ባኮስን እንዳስተማረው*

ልጆች! ጃንደረባው በወቅቱ የሚያነበው ቃል ትርጉሙ ስላልገባው ፊልጶስን እንዲያስተምረው ጠየቀው። ሐዋርያው ፊልጶስም ባኮስ የሚያነበውን መጽሐፍ ቅዱስ ተርጉሞ አስተማረው። ስለኢየሱስ ክርስቶስም ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን እና በመስቀል ተሰቅሎ እንዳዳነን ሰበከው። ጃንደረባውም በተማረው ትምህርት አመነ።

ከዚያም ወንዝ ወዳለበት ቦታ ሲደርሱ ጃንደረባው "እነሆ በውኃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ማን ነው?" ሲል ጠየቀው፤ ፊልጶስም "በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶልሃል" አለው። እርሱም፤ "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ" ሲልም ተናገረ። በኋላ ከሠረገላው ሁለቱም ወረዱ፤ ወደ ወንዙም ቀርበው ሐዋርያ ፊልጶስ ባኮስን አጠመቀው። ከውኃውም በወጡ ጊዜ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ወሰደው። ጃንደረባውም በመጠመቁ ደስ እያለው ጉዞውን ቀጠለ። (የሐዋ.ሥራ ፰፡ ፳፮-፴፱)

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ቅዱስ ባኮስ ከተጠመቀ እና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ከተቀበለ በኋላ ወደ ሀገሩ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ። ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰ በኋላ በተማረው መሠረት የቤተ መንግሥቱን ሰዎች ሁሉ በማስተማር አጠመቃቸው። በኢትዮጵያ ግዛትም እየተዘዋወረ ማስተማር ጀመረ። ከኢትዮጵያም በተጨማሪ በፐርሺያ፣ ሕንድ እና በሩቅ ምሥራቅ አገራት እየተዘዋረ ካስተማረ በኋላ በሰማዕትነት ዐረፈ።



*ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ ጃንደረባ ባኮስን እንዳጠመቀው፤*

ልጆች! ታሪኩን በደንብ ተከታተላችሁ አይደል? ጎበዞች! ከዚህ ታሪክ የምንማራቸው በርካታ ቁም ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በቅዱስ ፊልጶስ እና በቅዱስ ባኮስ አማካይነት መሆኑን፤ እኛም ደግሞ በየት ቦታ ስንሆን መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ እንደሚገባን፤ በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስን በደንብ ለመረዳት አባቶችን፣ መምህራንን መጠየቅ እንዳለብን፤ እንዲሁም በራሳችን መንገድ መጽሐፍ ቅዱስን መረዳትና መተርጎም እንደሌለብን እንገነዘባለን። ያልገባንን መጠየቅ፣ የተረዳነውን ደግሞ ለሌሎችም ማረዳትና ማስተማር እንዳለብን ጭምር ከዚህ ታሪክ እንማራለን። በሉ ልጆች፣ ለዛሬ በዚህ ይብቃን! በሚቀጥለው ጊዜ እስከምንገናኝ ድረስ ሰላመ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን፤ የሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ አማላጅነት፣ የቅዱስ ባኮስ በረከት ከሁላችን ጋር ይሁን፤ አሜን።

# ለሚመጣ ትውልድ ይጻፍ፥ (መዝ ፻፪፥፲፰)

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

ቤተ ክርስቲያን በየዘመናቱ የሚያጋጥሟት ፈተናዎች የሚደርሱባትም ጉዳቶች አሉ:: እነዚህ በታሪክ ዘመን ያጋጠሟት ፈተናዎችና የደረሱባት ጉዳቶች በታሪክ ተመዝግበው ትውልድ እንዲዘክራቸው ይደረጋሉ:: በዮዲት ጉዲት ጊዜ፣ በግራኝ አሕመድ ጦርነት ጊዜ፣ በጣልያን ወረራ ጊዜ ወዘተ እየተባለ የታረክ ዘመኑ ተጠቅሶ በምእመናንና በቤተ ክርስቲያን ቅርሶች ላይ የደረሰ ጉዳት ይተረካል:: በዚያ ታሪክን በጽሑፍ ለማስቀመጥ ቀናትና ወራት በሚፈጅበት ጊዜ እያንዳንዱ ክስተት ተመዝገቦ ለትውልድ እንዲቆይ የተጉ አባቶቻችን ምስጉኖች ናቸው::

ይህ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ የታወቀ ባህል ሆኖ የኖረ ነው::ለምሳሌም የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር ኢየሩሳሌምን ስላወደመበት ወረራ መጽሐፍ ቅዱስ የታሪክ ድርሳንም ሆኖ እንዲህ ይጽፍልናል፦

‹‹ሴዴቅያስም በነገሠ በዘጠነኛው ዓመት በዐሥረኛው ወር ከወሩም በዐሥረኛው ቀን የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆርና ሠራዊቱ ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው ከበቡአት፤… በከተማይቱ ራብ ጸንቶ ነበርና ለአገሩ ሰዎች እንጀራ ታጣ:: ከተማይቱም ተሸበረች፥ …. የከለዳውያንም ሠራዊት ንጉሡን ተከታተሉ፥ በኢያሪኮም ሜዳ ያዙት፤ ሠራዊቱም ሁሉ ከእርሱ ተለይተው ተበትነው ነበር:: ንጉሡንም ይዘው የባቢሎን ንጉሥ ወዳለበት ወደ ሪብላ አመጡት ፍርድም ፈረዱበት:: የሴዴቅያስንም ልጆች በፊቱ ገደሉአቸው፤ የሴዴቅያስንም ዓይኖች አወጡ፥ በሰንሰለትም አሰሩት፥ ወደ ባቢሎንም ወሰዱት:: ….. የባቢሎን ንጉሥ ባሪያ የዘበኞቹ አለቃ ናቡዛርዳን ወደ ኢየሩሳሌም መጣ:: የእግዚአብሔርንም ቤትና የንጉሡን ቤት አቃጠለ፤ የኢየሩሳሌምንም ቤቶች ሁሉ፥ ታላላቆቹን ቤቶች ሁሉ፥ በእሳት አቃጠለ::… የኢየሩሳሌምን ቅጥር ዙሪያዋን አፈረሱ::… በከተማይቱ ውስጥ የቀረውን ሕዝብ፥ ወይን ተካዮችና አራሾች እንዲሆኑ አስቀረ:: ከለዳውያንም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የነበሩትን የናስ ዐምዶች፥ በእግዚአብሔርም ቤት የነበሩትን መቀመጫዎችና የናስ ኵሬ ሰባበሩ፥ ናሱንም ወደ ባቢሎን ወሰዱ:: ምንቸቶቹንና መጫሪያዎቹንም መኰስተሪያዎቹንና ጭልፋዎቹንም የሚያገለግሉበትንም የናስ ዕቃ ሁሉ ወሰዱ:: የዘበኞቹም አለቃ ማንደጃዎቹንና መቀመጫዎቹን፥ የወርቁን ዕቃ ሁሉ በወርቅ፥ የብሩንም በብር አድርጎ ወሰደ:: ሰሎሞንም ለእግዚአብሔር ቤት የሠራቸውን ሁለቱን ዐምዶች አንዱንም ኵሬ መቀመጫዎቹንም ወሰደ፤ ለእነዚህ ዕቃዎች ሁሉ ናስ ሚዛን አልነበረውም::…. ታላቁን ካህን ሠራያን ሁለተኛውንም ካህን ሶፎንያስን ሦስቱንም በረኞች ወሰደ::… በከተማይቱም የተገኙትን በንጉሡ ፊት የሚቆሙትን አምስቱን ሰዎች፥ የአገሩንም ሕዝብ የሚያሰልፍ የሠራዊቱን አለቃ ጸሐፊ፥ በከተማይቱም ከተገኙት ከአገሩ ሕዝብ ስድሳ ሰዎች ወሰደ:: ወስዶ የባቢሎን ንጉሥ ወዳለበት ወደ ሪብላ አመጣቸው:: የባቢሎንም ንጉሥ መታቸው፥ በሐማትም ምድር ባለችው በሪብላ ገደላቸው:: እንዲሁ ይሁዳ ከአገሩ ተማረከ::…›› (፪ኛ ነገ ፳፭)

ይህን ስናስብ ዛሬም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እየደረሰባት ያለውን ፈተናና በፖለቲካ አለመረጋጋት ምክንያት በሀገር ውስጥ በሚካሄዱ የእርስ በእርስ ጦርነቶችና በውጪ ጣልቃ ገብነት ምክንያት እየተከሰቱ ባሉ ቀውሶች ከፍተኛ ጉዳት እያስተናገደች መሆኑ ጥያቄ የለውም:: በአንድ በኩል በግጭቱ ምክንያት ከየወገኑ ተዋጊ ሆነው በመሰለፍ ሕይወታቸውን በማጣት በሌላ በኩል ደግሞ በንብረትና በሀብታቸው ላይ በሚደርስ ጉዳት፣ በመፈናቀል/ስደት በሚያጋጥም እንግልት ቀዳሚ የጉዳት ተሸካሚ መሆናቸው አሌ አይባልም:: ከዚያም አልፎ የሀገር ቅርስ ሲወድም የመጀመሪያዋ የቅርስ ባለቤት ቤተ ክርስቲያን እንደመሆኗ ስቃዩ የከፋ ይሆንባታል:: በየአካባቢው ባሉ የፖለቲካ ውጥረቶች ሁሉ ባለፉት ሦስት ዓመታት ያስተናገደችው ጉዳት ቀላል የሚባል አይሆንም::

ይህንን ግን ጥቂትና ብዙ ብሎ ከመግለጽ ባለፈ እንደ ቀደሙ አባቶቻችን የደረሱ ዘርፈ ብዙ ጉዳቶችን ዕለት በዕለት መዝግቦ የሚያኖረው ማነው? የሚለው ጥያቄ ይሆናል::ጥያቄ ብቻ ሳይሆን በየጊዜው በሪፖርት መልክ በኦፊሴል የሚያሰማን አካል አለመኖሩ አስተዛዛቢ ነው::ከትግራይ እስከ ጎንደር፣ ከወሎ እስከ ሸዋ፣ ከሐረር እስከ ወለጋ፣ ከአርሲ እስከ ባሌ …በየምክንያቱ በክርስትያኖች ላይ የደረሰው ጉዳት ስንት ነው? ቆጣሪውስ ማነው? ገለልተኛ ሆኖስ በምን ደረጃ ተቋቁሟል ምን ያህልስ በቂ መረጃ ተገኝቶበታል? ጉዳቱ ብቻ ሳይሆን ምክንያትና ሂደቱስ በምን ደረጃ ታስቦበት ተዳሷል? የሚለው በውል መጠየቅ ያለበት ነው::

የመንግሥት አካላት የፈረሱ ትምህርት ቤቶችን የወደሙ መሠረተ ልማቶችን፣ የከሰረውን ኢኮኖሚ በጥናት ገምቶ በየጊዜው ይፋ እንደሚያደርገው ቤተክርስቲያን እየደረሰባት ያለውን ዘርፈ ብዙ ጉዳት ቢያንስ ለምእመናን

የምታሳውቅበት አሠራር ምን ያህል ተዘርግቷል? በውል አናውቅም፤ ነገሩ ትዝብት ላይ ይጥላል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ይህንን የምታደርገው እግዚአብሔር የሚቆጥረውን መከራ ሰው እንዲቆጥርላት ፈልጋ አይደለም፤ ነገር ግን ትውልድ በመከራ ሰንሰለት ውስጥ ይዞት የሚራመደውን ፈተና የሞላበትን ክርስትና እያወቀ፣ በተጋድሎ እየተሻገረ ለመጪው ትውልድ ትምህርት እንዲሆን ጽናትንም እንዲያሳይ ለማመላከት ነው፡፡ስለዚህ ጉዳታችን ስንት ነው ብሎ ቆጥሮ ሰፍሮ ማሳወቅ ከሚመለከተው ይጠበቃል፤ የሚመለከተው ካልሠራ ደግሞ ከትውልዱ ብርቱዎች የሚመለከታቸው ሆነው ተግባሩን ማከናወን ቢችሉ የሚያስባርክ ነው፡፡

የጌታን መከራ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በዐይኑ አይቶ እንደጻፈው የዐይን ምስክር ሆነው የቤተ ክርስቲያንን መከራ ካዩ ከሚመሰክሩ የመጀመሪያ ደረጃ ምንጭ ከሆኑ ሰዎች አጥርቶ የመከራው ልክ ሳይቃለል መጠናት፣ መመርመር፣ መጻፍ፣ ይፋም መደረግ አለበት፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ሊመጣ ያለውን የክርስቶስ የማዳን ሥራ በመንፈስ ትንቢት አስተውለው በእምነት ጽነተው ተጋድሎ ስለተቀበሉ ደጋጎች ‹‹የሚበልጠውን ትንሣኤ እንዲያገኙ እስከ ሞት ድረስ ተደበደቡ፤ሌሎችም መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ ከዚህም በላይ በእስራትና በወኅኒ ተፈተኑ፤ በድንጋይ ተወግረው ሞቱ፥ ተፈተኑ፥ በመጋዝ ተሰነጠቁ፥ በሰይፍ ተገድለው ሞቱ፥ ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ፤ ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ፥ በዋሻና በምድር ጕድጓድ ተቅበዘበዙ፡፡››(ዕብ ፲፩) እያለ መከራቸውን የቆጠረላቸው ዛሬ ተስፋውን ለጨበጡ ምእመናን የበለጠ ተጋድሎ እንዲያደርጉ ለማበርታት እነርሱንም መስለው የዚህን ዓለም ተገዳዳሪነት በድል እንዲሻገሩት ለመጽናት ነው፡፡

ስለዚህም የቤተ ክርስቲያን የዘመናችን መከራ በዝርዝር መመዝገብ፣ መጠናት መገለጽ አለበት የምንለው ለዚህ ነው፡፡የተቃጠሉ አብያተ ክርስቲያናት፣ የተገደሉ ምእመናን፣ የወደሙ ቅርሶች፣ የታጎሉ አገልግሎቶች፣ የተዘጉ አጥቢያዎች፣ የታወኩ ገዳማት፣ የተሰደዱ አገልጋዮችና ምእመናን፣ ለጦር ሜዳነት የዋሉ ቅዱሳት መካናት፣ የጠፋ ገጽታ፣ የተወጠኑ ሴራዎች፣ የከሸፉ የጥቃት ሙከራዎች፣ በጦርነት ያለቁ ምእመናን፣ በተዋጊነት ደማቸው በከንቱ የፈሰሰ ወገኖች ስንት ናቸው? ይህ በየጊዜው መከራው እስኪቆም በትጋትና በጥንቃቄ ሊሰነድ የሚገባው ታሪክ ነው፡፡

ብዙ ወገኖች እንዲህ ያለን ተግባር የሚጠብቁት ከጠቅላይ ቤተ ክህነት መሆኑ ይታወቃል፤ ይሁን እንጂ ጠቅላይ ቤተ ክህነት በዚህ ጉዳይ ስለሚያከናውነው ተግባር ፍንጭ የሰጠው ነገር ባለመኖሩ መጠበቅም ሆነ መረጃ በመስጠት መተባበር አያስችልም፡፡ ስለዚህ ተግባርን በውል ለማከናወን ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አካላት ድርሻ አላቸው፡፡

ምእመናን በየአካባቢያቸው ያለው የክርስቲያኖችን ሁኔታ፣ የቤተክርስቲያን የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ሁኔታ በውል ማጤን ይኖርበታል፡፡በተለይ ግጭትና ጦርነት ባለባቸው አካባቢዎች ያሉ ምእመናንን በግጭቱ የደረሱ የቤተ ክርስቲያን የሆኑ ጉዳዮችን በዝርዝር በማስታወሻ/ በጽሑፍ፣ በፎቶግራፍ፣ በድምፅ፣ .../ አደራጅተው መያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡ከተቻለ ደግሞ አጥቢያ አገልጋይ ካህናትና የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች መረጃዎችን በተደራጀ መንገድ ለመሰብሰብ ቢጥሩ ተግባሩን ፍሬያማ ያደርገዋል፡፡ እነዚህ ወገኖች ደግሞ የያዙትን መረጃ ከተቻለ ሊሰንዱ ለሚችሉ የቤተ ክህነቱ አካላት ወይም ይህን ተግባር ኃላፊነት ወስደው ለመሥራት እንቅስቃሴ ለሚያደረጉ አካላት እንደ ግብአት ማቅረብ ቢችሉ፣ ካልሆነም በማእከላዊነት ተግባሩ እስከሚከናወን መረጃውን በአግባቡ አደራጅቶ ማቆየት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ጠቅላይ ቤተ ክህነት ወይም ሀገረ ሰብከቶች፣ ማኅበራት... በዚህ ረገድ ሚናቸውን ለመወጣት የሚደርጉት እንቅስቃሴ በይፋ አለመታወቁ ችግር ሆኖ የሚታይና የሚያስተዛዝብ ነው፡፡ቢያንስ አስፈላጊ መሆኑን ባወቁበትና በተረዱበት ጊዜ እንኳን በአስቸኳይ ቢንቀሳቀሱ መልካም ነው፡፡

ይህ ካልሆነ የፈረሰውን ለማደስ፣ የተበላሸውን ለማስተካከል፣ ያዘነውን ለማጽናናት ወዘተ . . . መከናወን የሚገባቸውን ተግባራት ጽፎና መዝግቦ ማቆየት ይጠበቅብናል፡፡ለዛሬ ችግሩን ለመቅረፍ፣ ግንባታ ለማከናወን የሚጠብቀንን የገንዘብ፣ የሰው ኃይል፣ ዕውቀት፣ .... ፍላጎት ለመገመት ብቻ ሳይሆን ለቀጣዩም ትውልድ ማወቅ የሚገባውን የታሪኩን አሻራ በውል ለማኖር መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ ቀጣዩ ትውልድ መልካሙ ታሪክ ብቻ ደርሶት እልል እንዲል ብቻ ሳይሆን የዘመናችንንም የቤተ ክርስቲያን መከራ ዐውቆ እንዲማርበት እንዲጸናበት ይጻፍ፤ይጠና እንላለን፡፡

# ወንድሜን ላሳክመው ወይስ ላስጠምቀው?

## ክፍል ሁለት

ውድ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች! እንደምን ሰነበታችሁ? ስሜ ገብረ ኢየሱስ ይባላል የ፴ ዓመት ወጣት ስሆን በአንድ የግል ድርጅት ውስጥ ተቀጥሬ እየሠራሁ ራሴን እና ታናሽ ወንድሜን እያስተዳደርሁ እገኛለሁ፡፡ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ ስሆን ብዙ ጊዜም ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድን አዘወትራለሁ፡፡ ከተወሰኑ ጊዜያት ወዲህ ግን በወንድሜ ምክንያት ችግር ውስጥ ገብቻለሁ፡፡

ከእኔ ጋር የሚኖረው እና በሁለት ዓመት የምበልጠው ታናሽ ወንድሜ ችግር ውስጥ ነው፡፡ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ጠባዩ ሁሉ ተቀይሯል፡፡ ራሱን የሀገር መሪ አድርጎ ያስባል፤ ሁሉም ሰው ለሀገሩ ግድ የለውም በማለት ይኮንናል፡፡ በዚህም የተነሣ ራሱን የኢትዮጵያ አዳኝ እርሱ ብቻ ስለሀገር የሚገደው አድርጎ ያስባል፡፡ ከዕለት ዕለት በአመጋገብም ሆነ በአለባበስ ከሥርዐት እየወጣ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ እንቅልፍ ለመተኛት ይቸገራል፡፡ ሲብስበት ጠበል ወዳለባቸው ገዳማት ይዤው በመሄድ አንዳንዱ ጋር ለሰባት ቀን ሌሎች ጋር ደግሞ ፳፩ ቀናት አብሬው በመቀመጥ ለማስጠመቅ ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ ተማሪ ነበር፤ ትምህርቱን አቋርጧል፡፡ አንዳንዴ ገንዘብ ሲያገኝ ከቤት ወጥቶ አልኮል ጠጥቶ በአጉል ሰዓት እየመጣም ያስቸግረኛል፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ብዙ ሰዎችን ሳማክራቸው ጠበልና ጸሎትን እንዲያዘወትር ይመክሩኛል፡፡ ሌሎች ደግሞ የአእምሮ ሕክምና መስጫ ማእከላት እንድወስደው ይነግሩኛል፡፡ እኔ ደግሞ የአእምሮ ሕክምና የሚባለውን ነገር ለመቀበል ተቸገርሁ፡፡ ሁኔታዎች በተመቹ ሰዓት ጠበል ማስጠመቁን መርጫለሁ፡፡ ታናሽ ወንድሜ ዛሬም ችግሩ እየተባባሰበት ይገኛል፡፡ ውድ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች! ወንድሜን እንዴት ልታደገው እባካችሁ ምከሩኝ መልሳችሁን እጠብቃለሁ፡፡

ውድ ጠያቂያችን ገብረ ኢየሱስ! በቅድሚያ የገጠመዎትን እና ፈተና የሆነብዎትን ጉዳይ ይመለስልኛል፣ መፍትሔም አገኛለሁ ብለው ወደ እኛ በመጻፍዎ በእግዚአብሔር ስም ልናመሰግንዎ እንወዳለን፡፡

ገብረ ኢየሱስ ወደ እርስዎ ጥያቄ ከመግባታችን በፊት ደዌያትን በዓይነትና የሚከሠቱባቸውን ምክንያቶች በአጭሩ መዳሰስ ያስፈልጋል፡፡ ሰዎች በዚህ ዓለም ስንኖር በተጨባጭ የሚያጋጥሙንን የደዌ ዓይነቶች በሦስት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡ እነርሱም *ሥጋዊ* (አካለዊ)፣ አእምሯዊ (*ሥነ* ልቦናዊ) እና መንፈሳዊ ደዌያት ናቸው፡፡

እነዚህ ደዌያት በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ስናያቸው የሚከሠቱበት ምክንያትም አለ፡፡ በኃጢአት ምክንያት /ደዌ ዘኃጢአት/፣ በእግዚአብሔር ቊጣ ምክንያት /ደዌ ዘመቅሠፍት/፣ ጸጋን ክብርን ማግኛ የሆነው /ደዌ ዘዕሤት/ እና ከኃጢአት ለመንጻት የሚያበቃ ደዌ /ደዌ ዘንጽሕ/ ወዘተ. ብለን ልንጠቅሳቸው እንችላለን፡፡ በእነዚህና መሰል ምክንያቶች ሰዎች በአካለዊ፣ በመንፈሳዊ ወይም ደግሞ በአእምሮ መታወክ ደዌ ሊያዙ ይችላሉ፡፡

*ሥጋዊ* (አካላዊ) የምንለው ደዌ (ጉዳት) በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሱት መካከል እንኳን ብናይ ለምጽ፣ ትኩሳት፣ መድማት፣ ዐይነ ስውርነት፣ ዲዳነት ወዘተ. ማንሣት እንችላለን፡፡ *ሥነ* ልቡናዊ ስንል ደግሞ በስሜት መታወክ ምክንያት የሚመጡ አእምሯዊ ደዌ ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ደዌ በተለያዩ የስሜት መጎዳቶች ይከሠታሉ፡፡ እነርሱም ለምሳሌ ከፍተኛ ኀፍረት፣ *ሥጋት*፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ድንጋጤ፣ ኀዘን ወዘተ. ናቸው፡፡

የአእምሮ ሕመምን ብዙዎች እንደ ሕምም ለመቀበል ይቸገራሉ፡፡ ተራ የስሜት ችግር ይመስላቸዋል፡፡ ነገር ግን ሁላችን የምንጠቀምበት የዘመናዊው የሕክምናው ዓለም የአእምሮ ሕመሞችን በዓይነትና በደረጃ ከፍሎ ሰዎችን ከደዌው ለመፈወስ ይተጋል፡፡ የአእመሮ ሕምም ብልቶቻን ሁሉ ከሚታመሙበት መንገድ ለየት የሚያደርገው አስተሳሰብ/THINKING/፣ ስሜት /FEELING/፣ ጠባይ/ BEHAVIOR/ ላይ መዛባት ማስከተሉ ነው፡፡

ይህ ደዌ ቀላል/ጊዜያዊ/ ወይም ብርቱ/ጽኑ/ ሆኖ ሊከሰት ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት በጊዜያዊነት ወይም በዘላቂነት ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነትና ዕለት ዕለት በምንፈጽማቸው ተግባራት ላይ እክል ይፈጥራል፡፡ በእግዚአብሔር ረድኤት ወይም ለአካላዊ ደዌያት እንደምናደርገው ሕክምና ካልተገኘ ዘላቂ ሆኖ የሚቀጥል ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ሰዎች በራሳቸው ቤተሰብ ደርሶ ወይም በሕክምና ሳይንስ ውስጥ አልፈው የበሽታውን ባሕርይ ካላስተዋሉት ታማሚው ሆን ብሎ የሚፈጥረው አጉል ጠባይ ወይም መንፈሳዊ ደዌ ወይም ጊዜያዊ መረበሽ ይመስላቸዋል፡፡

ዘመናዊው ዓለም ለደዌያት የሚሰጠው ምክንያት ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ /ከመንፈሳውያን/ የተለየ እንደሚሆን ይታወቃል፡፡ አስቀድመን የጠቀስናቸውን የደዌ ምክንያቶች አለማወቁ ግን ለጊዜው የሕክምናው ዓለም ያስቀመጣቸው መፈወሻ ጥበቦች አንጠቀመም የሚያስብል ግን አይደለም፡፡ ለአካላዊ ደዌያት ምክንያቶቹ ምንም ይሁኑ ምንም

ለመታከም ከመንፈሳውያን አባቶች ጀምሮ ሁሉም የክርስቲያን ወገን እንደሚያደርገው ይጠበቃል:: የአእምሮ በሽታ /MENTAL DISORDER/ በሕክምናው ዓለም ዓይነቱና ምክንያቱ ብዙ ነው፤ ነገር ግን በመንፈሳውያን ዘንድ የሚጠቀሱ ምክንያቶችን ግን መነሻ አድርገን እንዳናስብ ደግሞ የሚከለክል አይደለም::

እንዲህ ዓይነቱ ደዌ በሌሎች ምክንያት ወይም በራሱ ምክንያት ሊከሠት የሚችል ነው:: በራሱ ከባድ ኃጢአት፣ ቅሌት ወዘተ. ምክንያት ሊሆን ይችላል:: ወይም ከባድ ተስፋ ማጣት ሲገባ የሚከሰት ነው:: ሰሎሞን በምሳሌው ‹‹የምትዘገይ ተስፋ ልብን ታሳዝናለች›› (ምሳሌ ፲፫፥፲፪) ያለው ዓይነት ማለት ነው:: ሰዎች በሆነ ተስፋ ውስጥ ሊቆዩ ይችላሉ:: ነገር ግን የያዙት ተስፋ እውን ሊሆን የማይችል (ከመጀመሪያውም ተስፋ መደረግ የሌለበት) ወይም እውን እንዲሆን በትጋት ያልሠሩለት ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የዘገየ ሲሆን ይህ ሊያጋጥም ይችላል:: ለከፍተኛ ድብርት ይዳርጋል:: ይህ በብዙ የዓለም ክፍሎች በሽታ ሆኖ ሰዎችን ራስን እስከ ማጥፋት ለሚያደርስ ድባቴ ያጋልጣቸዋል:: ምናልባትም የሥነ ልቦና ደዌ ከአካል ወይም ከሥጋ ደዌም የተነሣ ሊከሠት ይችላል::

የሕክምናው ዓለም ከሚጠቅሳቸው ምክንያቶች የጎሉትን ለማንሣት እንችላለን:: ከቤተሰብ ታሪክ ጋር በተያያዘ፣ በማኅፀን ሳለ ከሚያጋጥም መራዥ ነገር /TOXIC CHEMICALS/ ወይም የቫይረስ ጥቃት፣ እጅግ ከሚያሠቃየው የአእምሮ ቀዶ ጥገና፣ አልኮልና ሱስ አምጪ ነገሮችን አዘውትሮ ከመጠቀም፣ ብቸኝነት፣ ከልጅነት ሕይወት ጀምሮ ባለ የሕይወት ታሪክ ውስጥ ካጋጠመ ጥቃት እና ተከታታይ ጭንቀት፣ ሥነ ሕይወታዊ ምክንያት /CHEMICAL IMBALANCES IN THE BRAIN/፣ ፍርሃት/መንቀጠጥ የሚከሠት አመለካከት /PHOBIAS/.... እያለ ይዘረዝራል::

አስቀድምን ከጠቀስናቸው አካላዊና አእምሯዊ ደዌያት በላይ በጣም አደገኛና መዘዘኛ ደዌ መንፈሳዊ ደዌ/የርኵሳን መናፍስት ማደሪያ መሆን/ ነው:: ምክንያቱም የሰዎችን ሥጋዊ ሕይወት ብቻ ሳይሆን ዘለዓለማዊ የሆነውን የነፍስ ደዌ ስለሚሆን ነው:: ሦስተኛው ግን ከእነዚህ በተለየ በመንፈሳውያን ብቻ የሚታመንና ግልጽ የሆነ ደዌ ነው::

ይህ ደዌ ከላይ የጠቀስናቸውን ሁለቱንም ደዌያት ሊያስከትል ይችላል:: ለምንኖርበትም ዓለም ሥቃይ ሊወልድ ይችላል፤ ኑሮን አኗኗርን ሊያመሳቅል ይችላል:: ሁለቱ የሚከሠቱት መንፈሳዊ ደዌ ኃጢአትን ከመሥራት ጋር ስለሚያያዝ ከኃጢአት ሥራ በተገናኘ ለምሳሌ በማመንዘር ኤድስና የአባላዘር በሽታ ሊመጣ ይችላል:: ወይም ደግሞ ኃጢአት ቅጣት ወይም ፍዳ ሆኖ ሊመጣ ይችላል:: ቅጣት ሲሆን ተግሣጽ ወይም ምክርም ነው:: ለምሳሌ የሙሴ እኅት ማርያም እንዳጋጠማት የለምጽ በሽታ፤ ወይም በቤተሳይዳ በጌታ የተፈወሰው መጻጉዕ ታሪክ እንደሚያሳየን ማለት ነው:: (ዮሐ ፭)

ከኃጢአት የመነጨን ደዌ ለማራቅ፣ ለመፈወስ ግን የንስሓ ሕይወት የግድ ነው:: ይህንን ተስፋ የሚያደርጉ ሰዎች ግን የንስሓ ሕይወት ያስፈልጋቸዋል:: ከዚያም ብርቱ የጸሎት ሕይወት ያስፈልጋቸዋል:: የእምነት ሕይወት ያስፈልጋቸዋል:: የፍቅር ሕይወት ያስፈልጋቸዋል:: ይህንን መሠረት ያደረገ የምሥጢረ ቀንዲል ሥርዓት መፈጸምም ተገቢ ይሆናል:: ለማንኛውም ደዌ ግን እግዚአብሔር ፈውስን መስጠት ይችላል:: ዳዊትም ‹‹ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል፥ ደዌሽንም ሁሉ የሚፈውስ፥›› ይለዋልና (መዝ ፻፫፥ ፫)፤ ዳግመኛም ‹‹የአምላክህን የእግዚአብሔርን ቃል አጥብቀህ ብትሰማ፥ በፊቱም የሚበጀውን ብታደርግ፥ ትእዛዙንም ብታደምጥ፥ ሥርዓቱንም ሁሉ ብትጠብቅ፥ በግብፃውያን ላይ ያመጣሁትን በሽታ አላደርስብህም፤ እኔ ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነኝና›› (ዘጸ ፲፭፥ ፳፮) ይላል::

በሕክምናው ዓለምም የሚሰጠው በሽታን የመከላከል፤ ምርመራና ሕክምናም እግዚአብሔር ሰዎችን የሚጎበኝበት ሌላ መንገድ ነው:: ሐኪሞችን መሣሪያ አድርጎ በፈውስ የሚጎበኛቸው ብዙ ናቸው:: እንዲሁም በምድራውያን ሐኪሞች እጅ የማይቻለውንም የማይድን የሚመስል ደዌ በመፈወስም በግልጽ ተአምራትን የሚያደርግላቸው አሉ::

አስቀድመን የደዌያትን መከሠት ምክንያቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አድርገን ስናነሣ እንደጠቀስነው ደዌ ለበጎ ወይም ለመጥፎ ሊሆን ይችላል:: ለጉዳት ወይም ለክብር ሊሆን ይችላል:: ለበጎ ወይም ለመጥፎ የሚሆነው የባለደዌው አረዳድና አቀባበል እምነት ነው:: በደዌ ተስፋ አለመቁረጥን ከኢዮብ መማር ያስፈልጋል:: (ኢዮ. ፪፥ ፱) ቅዱስ ጳውሎስም ምሳሌያችን ነው:: (፩ኛቆሮ. ፲፪፥ ፱-፲)::

ጠያቂያችንም በጥያቄዎ እንዳነሡት፣ ለወንድምዎ ችግር መፍትሔ ይሆናል ብለው ከወዳጅ ዘመድ የተሰጠዎ የተለያዩ ምክሮች ይኖራሉ:: ለወንድምዎ ችግር ጸሎትና ጠበልን መፍትሔ አድርገው ምክር የሰጡት ሰዎችም ሆኑ ወደ አእምሮ ሕክምና እንዲወስዱት ምክር የሰጡ ወዳጆችዎ አልተሳሳቱም::

በጸሎት፣ በጾም፣ በጠበል ብዙዎች ከየትኞቹም ችግሮቻቸው ይፈታሉ:: እነዚህ መንፈሳዊ መፍትሔዎች እንደ እምነታችን ጥንካሬ እንደ እግዚአብሔርም ፈቃድ የትኞቹንም ዓይነት ደዌያት ሊፈውሱ ይችላሉ:: ስለዚህ ለወንድምዎ ችግር ጠበልን፣ ጸሎትን መፍትሔ አድርገው መያዝዎን መቀጠል አለብዎት:: ከላይ በጥያቄዎ ለማንሣት

እንደሞከሩት ወደ ተለያዩ ገዳማት ወንድምዎን ይዘው መሄድዎ በጎ ሆኖ ሳለ ብዙ ቦታ ወስጄው ለውጥ ግን አላሳየም ብለው ተስፋ መቁረጥ የለብዎትም። እግዚአብሔር ሰዎችን የሚፈውስበት የራሱ ጊዜ አለውና በሰባትና በ፳፰ ቀን ሱባኤ ብቻ ወንድሜ አልተፈወሰም ብለው ማሰብዎ ሰዎች ያቀረቡልዎት አማራጭ መፍትሔ ውስጥ ገብተው እንዲዋልሉ ሆነዋል። ይህ ማለት ግን የወንድምዎ ችግር የአእምሮ ሕመምን ሊሆን እንደሚችልና ሐኪም ማማከር እንዳለብዎ ምክር የለገሱ ወዳጆችዎንም ለምን ሰሙ ማለትም አይደለም።

በመሆኑም በወንድምዎ የደረሰው ችግር መነሻውን ምክንያቱን በውል ማጤን ከእርስዎ ይጠበቃል። ‹‹ጠባዩ ሁሉ ተቀይሯል። ራሱን የሀገር መሪ አድርጎ ያስባል፤ ራሱን የኢትዮጵያ አዳኝ አድርጎ ያስባል። ከዕለት ዕለት በአመጋገብም ሆነ በአለባበስ ከሥርዐት እየወጣ ነው። ብዙ ጊዜ እንቅልፍ ለመተኛት ይቸገራል። ትምህርቱን አቋርጧል። አንዳንዴ ገንዘብ ሲያገኝ ከቤት ወጥቶ አልኮል ጠጥቶ በአጉል ሰዓት እየመጣም ያስቸግረኛል።›› በማለት የዘረዘሯቸው ምልክቶች ሁሉ የአእመሮ ሕሙማንም የሚያሳዩአቸው ምልክቶች ስለሆኑ ወዳጆችዎ ወንድምዎን ወደ ሕክምና እንዲወስዱ መምከራቸው አሳማኝ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም እንደ ሥጋዊ አካላችን ሁሉ አእምሯችንም በተለየ ጸጋ ካልሆነ በስተቀር መሸከም የማይችላቸው ከባድ ስሜት የሚፈጥሩ ሐሳቦች፣ ድርጊቶችና ክሥተቶች ሊየጋጥሙት ይችላሉ። ለፍላጎታችን ገደብ ካላበጀንም የማንቆጣጠረው የምኞት ደረጃ ላይ ያደርሰናል። ለማወቅ ያለንም እርምጃ ከልኩ ካለፈ እንዲሁ።

ወንድምዎ ምክንያቱን በሚያውቁት ወይም በማያውቁት ምክንያት ለአእመሮ ሕመም ተጋልጠው ከሆነ በጸሎትና በጠበል መትጋት ተገቢ ነው። ከላይ በጠቀሱት ጥቂት ጊዜ ወንድሜ አልተፈወሰም በማለት በእግዚአብሔር ላይ ተስፋ መቁረጥ አይገባም። በዮሐንስ ወንጌል ምእራፍ ፭ ላይ ታሪኩ ተጽፎ የምናገኘው የመፃጉዕ ሕይወት አብነት ማድረግ ይገባል። ይህ ሰው ለ፴፰ ዓመታት በቤተ ሳይዳ መጠመቂያ ቦታ ተኝቶ የነበረው መጻጉን የመዳኑን ቀን ይጠባበቅ የነበረ፣ ከአልጋው ተጣብቆ የሚኖር በሽተኛ ነው። ሆኖም እግዚአብሔር በፈቀደው ጊዜ መፃጉዕ አልጋውን በራሱ ተሸክሞ እስኪሄድ ድረስ ፍጹም ፈውስን ሰጥቶታል። አንተም በእምነት እና እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ በጠበሉ ብትተጋ የወንድምህን ፍጹም ደኅንነት ማየትህ አይቀርም። እግዚአብሔር ፍጹም መሐሪ፣ ይቅር ባይ ነውና ወንድምህን ይፈውሰዋል። ከጠበሉ ጎን ለጎን የአእመሮ ሕክምናም ቢከታተሉ ኃጢአት አይደለም።

ጠያቂያችን ሊያውቁት የሚገባው ቁም ነገር፣ እግዚአብሔር በአንድም ወይም በሌላ መፍትሔን እንደሚሰጥ ማመን ተገቢ መሆኑን ነው። የአእምሮ ሕመምንም እግዚአብሔር ይፈውሳል። እግዚአብሔር ራሱ ይሠራል፤ እግዚአብሔር በልጆቹ ይሠራል፤ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ሁሉ ሊሠራ ይችላል። ሰዎች ሥጋዊ ሕመም ሲታመሙ ወደ ሐኪም ይሔዳሉ፤ እግዚአብሔርም ፈውሱን እንዲሰጣቸው ይጸልያሉ። የሰዎችን አእምሮ የፈጠረው እግዚአብሔር ነው። የሚያስቡበትን ልክ እንደሰጠ ሁሉ የጥበብ ሐሳብ ምንጭ አድርጎም ነው። ስለዚህ የሥጋ ጉልበታችን ለበጎ እንደምንጠቀምበት ሁሉ አእምሮአችንንም እንጠቀምበታለን። ስለዚህም ከእርሱ የሚሰጠንን አዲስ ጸጋ ብቻ ሳይሆን የሰጠንን በውስጣችን የፈጠረውን፣ የገለጸልንን ያጎናጸፈን ሀብት ሁሉ መጠቀም አለብን።

እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ፣ ክህሎት፣ ዕውቀት ተጠቅመው በሙያ የሚያገለግሉ በርካታ ሰዎች አሉ። ምድራዊ ሕይወትን ከባለሙያዎች ውጪ ማሰብ ከባድ እንደሆነ ሁሉ፤ ይህንንም ሞያ መቀበልና ማክበር ከእርሱም የተሰጠን ጸጋ መጠቀም ያስፈልጋል። የምድርን ሕይወት በሆነም መጠን ቢሆን በአቅማችን ማረጋጋት የምንችለው ሞያዎች ሁሉ በአግባብና በሥርዓቱ ጥቅም ላይ ሲውሉ ነው።

ብዙ ሰዎች የአእምሮ ሕመምን በራስ የሚፈታ ችግር ብቻ አድርገው ያስባሉ። የአእምሮ ሕክምና ባለሙያዎችንም እንደማያስፈልጉ የሚያስቡ አሉ። ጸሎት ግን የሐኪምን ሙያ እንዳንጠቀም አይከለክልም፤ በአንጻሩም ሕክምና ላይ ብቻ ችክ ብሎ የእግዚአብሔርን የማዳን ክንድ ችላ ማለት ራስን ለአላስፈላጊ ጉዳት መዳረግ ነው። በምድራችን ላይ ብዙዎች ቀን ተቀጥሮላቸው ትሞታላችሁ፣ ተስፋ የላችሁም ከተባሉ በኋላ በእምነትና በጠበል ድነው ረጅም እድሜን ኖረዋል። አንዳንዶችም የቀዶ ጥገና ካልተደረገላችሁና ካልወጣላችሁ ለሕይወታችሁ አስጊ ነው ከተባሉ በኋላ ጠበል ጠጥተውና እምነት ተሻሽተው ትእዛዝ የሰጧቸው ሐኪሞች እስኪደነቁ ድረስ ደዌያቸው ጠፍቶላቸው ፍጹም ተፈውሰው ተገኝተዋልና የእግዚአብሔርን የማዳን ኃይል በእምነት መቀበል ተገቢ ነው።

ስለዚህ ውድ ጠያቂያችን መገንዘብ ያለብዎ የተሰበረ አካል በአካላዊ ቴራፒ እንደሚጠገን እንደሚመለስ ሁሉ፣ የአእምሮ ሕሙማንም ከተዛነፈ የሐሳብ ሥብራታቸው እንዲፈወሱ አእምሯዊ ቴራፒ አለ። ያንን መጠቀም አይነቀፍም። ይህንን ሲያደርጉ ግን የሐኪምን ምክርና ሕክምናን ምክንያት አድርጎ ትልቁን እና የሚበልጠውን እግዚአብሔር ይፈውስ መሻትና መጠቀም እንዲሁም ለራስም ሆነ ለሌላ ሰው መጸለይና መንፈሳዊ ትጋቶችን አብሮ ማስኬድ ይገባል።

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር***